# የጳውሎስ ነገረ-መለኮት

## ትምህርት ሁለት

## ጳውሎስ እና የገላትያ ሰዎች

# The Heart of Paul's Theology

## Lesson Two

## Paul and the Galatians

ተርጓሚ እሸቴ በለጠ

Translator: Eshete Belete

THIRD MILLENNIUM MINISTRIES

Biblical Education. For the World. For Free.

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

# እናስተዋውቅዎ

የሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ1997 ዓ.ም. ተመሠረተ፡፡ ይህ አገልግሎት አትራፊ ያልሆነ ድርጅት ሲሆን፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎችን ለመላው ዓለም በነጻ ለማዳረስ የተቋቋመ ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለውን ጤናማ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ - መሠረት ያለው ክርስቲያናዊ የአመራር ስልጠና ፍላጎት ምላሽ ለመስጠት፣ ምንም ዓይነት የስልጠና ግብዓቶች የማግኘት እድል ለሌላቸው ክርስቲያን መሪዎች የሴሚነሪ ሥርዓተ-ትምህርቶችን በማዘጋጀት እናሰራጫለን፡፡ ሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ በመላውም ዓለም ለሚገኙ ክርስቲያን መሪዎችና ፓስተሮች የተመጣጠነ ዋጋ ያለው፣ በደጋፊዎች የሚታገዝ፣ ለተጠቃሚው ምቹ፣ በልዩ ልዩ የመገናኛ ብዙሃን ዘዴዎች የታገዘ ሥርዓተ-ትምህርት በአምስት ቋንቋዎች (በእንግሊዝኛ፣ በስፓኝ፣ በራሺያኛ፣ በማንዳሪን ቻይንኛ እና በአረብኛ) አስተርጎሞ አሰራጭቷል፡፡ ሁሉም ትምህርቶች የተጻፉት፣ የተዘጋጁት እና የታተሙት በአገልግሎቱ ውስጥ ሲሆን በ The History Channel©. In 2009 ካሉት ጋር በቅርፅና በጥራት ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ የሰርድ ሚሊኒየም ሥራ ማለትም ጥራት ላለው የማስተማሪያና የአኒሜሽን የቪዲዮ ፕሮዳክሽን ሥራዎቹ ሁለት የቴሊ አዋርድ ሽልማቶችን ተቀብሏል፡፡ የማስተማሪያ ግብዓቶቻችን በዲቪዲ፣ በህትመት፣ በኢንተርኔት ማስተላለፊያ ዘዴዎች፣ በሳተላይት የቴሌቪዥን ስርጭት፣ በራዲዮና በቴሌቪዥን ስርጭቶች ለማቅረብ በሚያስችል መልክ የተቀረፁ ናቸው፡፡

ስለ አገልግሎታችን የበለጠ መረጃ ለማግኘትና እንዴት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን እንደምትችሉ ማወቅ ከፈለጋችሁ፣ www.thirdmill.org የተሰኘውን ድረ-ገጽ ይጎብኙ፡፡

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

# ማውጫ


1. **መግቢያ**
2. **ዳራ**
    - የመጀመሪያ ጉዞ
    - ችግሮች
        - የአህዛብ በብዛት መጨመር
        - የሐሰት መምህራን
3. **ይዘት**
    - ቅድመ ጽሑፍ/ድኅረ ጽሑፍ
    - የችግሩ መግቢያ
    - ታሪካዊ ዳራ
        - ጥሪና ስልጣና
        - ከመሪዎች ጋር መገናኘት
        - ከጴጥሮስ ጋር መፋለም
    - ነገረ-መለኮታዊ ማስረጃ
        - ቀደምት ልምድ
        - የአብርሃም እምነት
        - የወቅቱ ልምድ
        - የአብርሃም ሚስቶችና ወንዶች ልጆች
    - ተግባራዊ ማሳሰቢያ
        - በክርስቶስ ነፃ መውጣት
        - የመንፈሱ ኃይል
        - መለኮታዊ ፍርድ
4. **ነገረ-መለኮታዊ አመለካከቶች**
    - ክርስቶስ
    - ወንጌል
    - ሕግ
    - ከክርስቶስ ጋር አንድ መሆን
    - መንፈስ ቅዱስ
    - አዲስ ፍጥረት
5. **ማጠቃለያ**


© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

# 1. መግቢያ

በአንድ ወቅት ገና በለጋነት ዕድሜዋ ስላገባች አንድ ሴት ታሪክ ሰምቼ ነበር፡፡ ገና በጣም ለጋ ወጣት በመሆኗ፣ ለአዲሱ የአዋቂነት ሕይወት ዝግጁ አልነበረችም፡፡ ብዙም ሳትቆይ፣ በብዙ መጨነቅ ጀመረች፣ እናም የተለመደውን የልጅነት ሕይወት ምቾት ማጣት ጀመረች፡፡ ስለዚህም፣ አንድ ቀን ባለቤቷ ሥራ ሄዶ ሳለ፣ ወደ ወላጆቿ ጓሮ ሹልክ ብላ ገባችና በቀደመው የመጫወቻ ቤቷ ውስጥ ተደበቀች፡፡ ባለቤቷም በዚያ ምሽት በተደበቀችበት ሲያገኛት፣ የሚንቀጠቀጡ እጆቿን ያዝ አድርጎ፣ በእርጋታ ወደ ቤቷ መለሳት፡፡ ለእርሷ አሁን እንደ አዋቂ መኖር እንደሚቸግራት ያውቃል፣ ሆኖም ደግሞ የልጅነት ዘመኗን ልትሰናበተው እንደሚገባም ያውቃል፡፡ በሕይወቷ አዲስ ቀን እየመጣ ነው፣ እናም የአዋቂነትን ሕይወት ድንቃ ድንቆችና ተግዳሮቶች ከባለቤቷ ጋር ልትጋፈጥና ደስ ልትሰኝባቸው ይገባል፡፡

በመጀመሪያውም ክፍለ ዘመን፣ ቤተክርስቲያንንም ተመሳሳይ ነገር ገጥሟታል፡፡ አብዛኞቹ ቀደምት ክርስቲያኖች አይሁዳውያን የነበሩ ሲሆን በሃይማኖት ወጎችና በጁዳይዝም ህግጋት ሞግዚትነት ስር እያደጉ ያሉ ሰዎች ነበሩ፡፡ ሆኖም እነዚህ አይሁዶች ክርስቶስን መከተል ሲጀምሩ፣ ከእግዚአብሔር ጋር የነበሯቸው ግንኙነቶች ተለወጡ፡፡ ከዚያም በክርስቶስ አማካይነት የእግዚአብሔርን ሙሉ መገለጥ ስላገኙ ወደ መንፈሳዊ በሳልነት የሕይወት እርከን አደጉ፡፡ ሆኖም ጥቂት ቆይተው፣ እነዚህ ቀደምት አይሁዳውያን ክርስቲያኖች የለመዱትን የአሮጌውን የአይሁድ ልምምዳቸውን ሲያጡ ምቾት አልሰማ ይላቸው ጀመር፣ ስለዚህ የክርስትና እምነታቸውን አሁን እየተዉት ካለው አይሁዳዊ ልማዳቸው ጋር መቀየጥ ጀመሩ ሌሎችም ያንኑ እንዲያደርጉ ያስገድዱ ጀመር፡፡

የጳውሎስ ነገረ-መለኮት ከተሰኘው ተከታታይ ትምህርታችን ይህ ሁለተኛው ትምህርት ሲሆን ርዕሱንም “ጳውሎስና የገላትያ ሰዎች” ብለነዋል፡፡ በዚህ ትምህርት፣ የገላትያ አብያተክርስቲያናት የጁዳይዝምን አንዳንድ ልምምዶች እንደገና እንዲያንሰራሩ በማድረግ ወደ መንፈሳዊ ሕፃንነት መመለሳቸውን እንመለከታለን፡፡ ደግሞም ጳውሎስ ከእነዚህ ወደ ኋላ እየተመለሱ ካሉ ክርስቲያኖች ጋር እንዴት እንደተፋለመም እናያለን፡፡

ጳውሎስና የገላትያ ሰዎች የተሰኘው ጥናታችን በሦስት ክፍሎች ይከፈላል፡፡ በመጀመሪያ፣ ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች የጻፈውን መልእክት ዳራ እንመለከታለን፡፡ ሁለተኛ፣ ለገላትያ ሰዎች የጻፈውን መልእክት ይዘት እናያለን፡፡ ሦስተኛ ደግሞ፣ ደብዳቤው የጳውሎስን ነገረ-መለኮታዊ አመለካከት ማዕከላዊ ሃሳብ ማለትም፣ የመጨረሻው ዘመን አስተምህሮውን ወይም ነገረ-ፍፃሜውን፣ እንዴት እንደገለጠው እንመረምራለን፡፡ አስቀድመን ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች የጻፈውን መልእክት ዳራ እንመልከት፡፡

# 2. ዳራ

ጳውሎስ መልእክቶቹን የጻፈው ከቦታ ቦታ በሚዘዋወርበት ወቅት ነው፡፡ ስለዚህም፣ ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች የጻፈባቸውን ጉዳዮች ለመረዳት፣ በገላትያ የነበረውን ታሪካዊ ሁኔታ ለመረዳት የሚያግዙንን ጥቂት መሠረታዊ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት ያስፈልገናል፡፡ ይህንን ጉዳይ በሁለት መንገዶች እንዳስሰዋለን፡፡ በመጀመሪያ፣ ጳውሎስ በመጀመሪያ ሚሲዮናዊ ጉዞው ከገላትያ ዘዎች ጋር የነበረውን ግንኙነት እንከልሳለን፡፡ ሁለተኛ ደግሞ፣ ጳውሎስ ለእነርሱ እንዲጽፍላቸው ያነሳሱትን ጥቂት ችግሮች እንመለከታለን፡፡ አስቀድመን የጳውሎስ የመጀመሪያ ሚሲዮናዊ ጉዞ ዳራ እንመልከት፡፡

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

# ሚሲዮናዊ ጉዞ

ይህ ጉዞ የጀመረው በ 46 ዓ.ም. እግዚአብሔር ጳውሎስንና በርናባስን ለተለየ ሚሲዮናዊ አገልግሎት ለዩልኝ ብሎ ለሶርያዋ አንጾኪያ ቤተክርስቲያን ከተናገረ በኋላ ነበር፡፡ ጳውሎስና በርናባስም ወደ ቆጵሮስ በመርከብ በመጓዝ ጉዟቸውን ጀመሩ፡፡ በምስራቃዊቷ ከተማ በሳላሚስ ጀምረው፣ ከምኩራብ ወደ ምኩራብ በመዘዋወር ወንጌልን እየሰበኩ ወደ ምዕራባዊቷ ከተማ ጳፉ አመሩ፡፡

ጳውሎስና በርናባስ ከቆጵሮስ ነስተው በመርከብ ወደ ጴርጌ አቀኑ፣ ከዚያም በምድር ወደ ጵስድያዋ አንጾኪያ ሄዱ፣ ያችም ምድር በዚያን ወቅት የሮሜ ግዛት የነበረችው የገላትያ ክፍል ነበረች፡፡ በዚያም ስፍራ ጳውሎስ በምኩራብ የሰበከውን የወንጌል መልእክት ያደመጡ በርካታ አይሁዶች አዎንታዊ ምላሽ ሰጡ፡፡ ሆኖም በሳምንት ውስጥ፣ የማያምኑት አይሁድ በጳውሎስና በበርናባስ ላይ ከተማውን አስነሱባቸው፣ ከከተማውም ገፍተው አስወጧቸው፡፡

ጳውሎስና በርናባስም ከጵስድያዋ አንጾኪያ ተነስተው፣ ወደ ሩቅ ምሥራቅ ወደ ገላትያ ግዛት ተጓዙ፣ ከዚያም በመጀመሪያ በኢቆንዮን ከተማ አረፉ፡፡ በዚያም በምኩራብ መስበክ ሲጀምሩ፣ በርካታ አይሁዶችና አህዛብ ወደ እምነት መጡ፣ ሆኖም ግን ቤተክርስቲያኒቱ ጸንታ አልቆመችም ምክንያቱም ያላመኑ አይሁዶች ሊገድሏቸው ስላሴሩ ጳውሎስና በርናባስ ከተማይቱን ፈጥነው በመልቀቃቸው ነው፡፡

ቀጥለው ያረፉት በልስጥራ ከተማ ሲሆን፣ በዚያም ጳውሎስ ሌላ ቤተክርስቲያን ተከለ፡፡ በልስጥራ፣ ከመወለዱ ጀምሩ ሽባ የነበረ ሰው በጳውሎስ አገልግሎት ወቅት ተፈወሰ፡፡ የከተማይቱ ሰዎች ይህንን ተዓምራት ሲመለከቱ ግን፣ ጳውሎስን ሄርሜስ በርናባስን ደግሞ ዜየስ የሚል የአማልክት ስያሜ በመስጠት ሊያመልኳቸው ሞከሩ፡፡ ለሚስዮናውያንም ሊሰዉላቸው ሞከሩ፣ ጳውሎስና በርናባስ ግን እንደነርሱው ሰዎች መሆናቸውን አብራሩላቸው፡፡ ከዚያም በኋላ፣ አንዳንድ ያላመኑ አይሁድ ከኢቆንዮን መጡ፣ ግራ ተጋብተው የነበሩትን የኢቆንዮን ዜጎች በጳውሎስና በበርናባሰ ላይ አነሳሱባቸው፣ እግዚአብሔር ግን የጳውስን ሕይወት አተረፈ እርሱም ከዚያ ወደሌላ ሄደ፡፡ ጳውሎስና በርናባስም በስተምሥራቅ ወደ ገላትያና ወደ ደርቤ ተጓዙ፣ በዚያም በርካቶች ክርስቶስን አመኑ፡፡ በደርቤም፣ ጳውሎስ ሽማግሌዎችን በመሾም ቤተክርስቲያንን አደራጀ፡፡

ጳውሎስ ግን አሁንም በልስጥራ፣ በኢቆንዮን እና በጵስድያዋ አንጾኪያ ለሚገኙ ክርስቲያኖች እጅግ ግድ ይለዋል፡፡ ስለዚህም፣ ጳውሎስና በርናባስ ሕይወታቸውን ለአደጋ አጋልጠው በመስጠት፣ ወደ እነዚህ ከተሞች ተመልሰው ሄዱ፡፡ ገና ያልበረቱ የነበሩትን አብያተክርስቲያናት በማበረታታት እና በጳውሎስና በበርናባስ ላይ እየሆነ ያለው መከራና ስቃይ ሁሉም አማኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት ሲያስፉ የሚቀበሉትና ሊጸኑበት የሚገባ እንደሆነ አብራሩላቸው፡፡ ሚሲዮናውያኑም ከጵስድያዋ አንጾኪያ ተነስተው፣ ወደ ወደብ ከተሞች በማቅናት በፍርግያና፣ በአጣሊያ ከተሞች ሰበኩ፡፡ ከአጣሊያም፣ ወደ ሶርያዋ አንጾኪያ በመከርከብ ተጓዙ፡፡

ጳውሎስ በገላትያ መጽሐፍ ውስጥ፣ በገላትያ ስለነበረው ጊዜ ይጠቅሳል፡፡ ስለዚህ፣ ይህንን መልእክት የጻፈው፣ ከመጀመሪያው ሚሲዮናዊ ጉዞው በኋላ እንደሆነ እንረዳለን፡፡ ሆኖም ይህ ለገላትያ ሰዎች የተጻፈ መልእክት በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 15 የተመዘገበውንና እውቅ የሆነውን ቆየት ብሎ የተከናወነውን የኢየሩሳሌሙን የሐዋርያት ጉባዔ አለመጥቀሱን ማንሳት ጠቃሚ ነው፡፡ የኢየሩሳሌሙ ጉባዔ ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች ያነሳቸውን አንዳንድ ጉዳዮች የኢየሩሳሌሙ ጉባዔም ዳስሷቸዋል ምናልባትም ጉባዔው የገላትያ መልእክት ከመጻፉ በፊት ተካሂዶ ከሆነ ጳውሎስ ለአመለካከቶቹ ድጋፍ ለማግኘት ሲል እነዚህን ጉዳዮች ለጉባዔው አቅርቦ ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ ነገሩ የሚመስለው የገላትያን መጽሐፍ የጻፈው በ48 ዓ.ም. ሲሆን፣ ገላትያን ለቆ ከሄደ ከዓመት በኋላ አካባቢ፣ ሆኖም የኢየሩሳሌም ጉባዔ ከመካሄዱ አስቀድሞ እንደሆነ ነው፡፡

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

የገላትያ መጽሐፍ ከጳውሎስ የመጀመሪያ ጉዞ ጋር እንዴት እንደሚዛመድ ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ ጳውሎስን አሳስበውት የነበሩና በገላትያ የነበሩ ችግሮችን እንመለከታለን፡፡

# ችግሮች

የገላትያ አብያተክርስቲያናት የነበሩበት ሁኔታ ምን ነበር? በእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት የነበሩና ጳውሎስን እንዲጽፍ የቀሰቀሱት ጉዳዮች ምንድን ናቸው? ሁለት ጉዳዮችን እንዳስሳለን፣ እነርሱም፡ወደ አብያተክርስቲያናት በብዛት የጎረፉት አህዛብ እና የሐሰት መምህራን ማቆጥቆጥ ናቸው፡፡ አስቀድመን አህዛብ ክርስቲያኖች ወደ ገላትያ አብያተክርስቲያናት የጎረፉበትን ሁኔታ እንዳስስ፡፡

## የአህዛብ በብዛት መጉረፍ

እግዚአብሔር በጳውሎስ የመጀመሪያ ሚሲዮናዊ ጉዞ ካከናወናቸው ታላላቅ ነገሮች አንዱ በርካታ አህዛብን ወደ ክርስቶስ ማምጣት ነበር፡፡ ጳውሎስን እጅግ በጣም ባስገረመው መንገድ፣ በገላትያ የሚኖሩ አይሁዶች ወንጌልን ተቃወሙ፡፡ ጳውሎስ ከዚህ መጠነ ሰፊ ተቃውሞ ጋር ሲጋፈጥ፣ አህዛብን እንዲደርስ እግዚአብሔር እንደፈለገ ጳውሎስ እየተረዳ መጣ፡፡ በሐዋርያት ሥራ 13፡46-47 በጵስድያዋ አንጾኪያ ለሚገኙ አይሁዶች የተናገራቸውን ቃሎች እናድምጥ፡

> ***ጳውሎስና በርናባስም ገልጠው፦ የእግዚአብሔር ቃል አስቀድሞ ለእናንተ ይነገር ዘንድ ያስፈልጋል፤ ከገፋችሁትና የዘላለም ሕይወት እንዳይገባችሁ በራሳችሁ ከፈረዳችሁ ግን፥ እነሆ፥ ወደ አሕዛብ ዘወር እንላለን።***
> ***እንዲሁ ጌታ፦ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ለማዳን ትሆን ዘንድ ለአሕዛብ ብርሃን አድርጌሃለሁ ብሎ አዞናልና አሉ። (የሐዋርያት ሥራ 13፡46-47)***

ይህ ምንባብ በጳውሎስ አገልግሎት ውስጥ ትልቅ የአቅጣጫ ለውጥ መካሄዱን ይገልጣል፡፡ እንደ አይሁድነቱ፣ ለአይሁድ ወንጌል ማድረስን አስቀድሟል፡፡ ሆኖም ለወንጌል የነበራቸው አሉታዊ ምላሽ አህዛብን እንዲደርስ እግዚአብሔር እየጠራው እንደሆነ እንዲያምን አድርጎታል፡፡ ይህንንም በብዙ ስኬት አከናውኖታል፡፡ ጳውሎስ በኢቆንዮን ያከናወነውን ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ 14፡1 ላይ እንዴት ጠቅለል አድርጎ እንዳቀረበው እናድምጥ፡

> ***በኢቆንዮንም እንደ ቀድሞ ወደ አይሁድ ምኩራብ ገብተው ከአይሁድና ከግሪክ ሰዎች ብዙ እስኪያምኑ ድረስ ተናገሩ። (የሐዋርያት ሥራ 14፡1)***

ወደ እምነት የመጡት አይሁዶች ብቻ አይደሉም፣ አህዛብም ጭምር ናቸው፡፡

በተመሳሳይም መንገድ፣ በሐዋርያት ሥራ 14፡27 ውስጥ ጳውሎስ የመጀመሪያውን ሚሲዮናዊ ጉዞ ጠቅለል ያደረገበትን ተግባር ሉቃስ እንዲህ ዘግቦታል “እግዚአብሔር … ለአሕዛብም የሃይማኖትን ደጅ እንደ ከፈተላቸው ተናገሩ።” ምናልባት በርካታ አህዛብ አማኞች በገላትያ አብያተክርስቲያናት ውስጥ በመታየታቸው ሁሉም ሰው ደስ ብሎታል ብለን እናስብ ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን የአህዛብ መጉረፍ በገላትያ ውስጥ በርካታ ችግሮችን ቀስቅሷል፡፡ እነዚህም ችግሮች የአይሁድ የሐሰት መምህራን በተቃውሞ እንዲነሱ ቀስቅሷቸዋል፡፡

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

## የሐሰት መምህራን

የጳውሎስ የመጀመሪ ሚሲዮናዊ ጉዞ እስከጀመረበት ጊዜ ድረስ፣ የክርስቲና ቤተክርስቲያን በተቀዳሚነት የአይሁድ ነበረች፡፡ የመጀሪያዪቱ ቤተክርስቲያን የተጀመረችው በኢየሩሳሌም ነበር እናም ከአይሁድ ማንነት ጋር በብርቱ የተቆራኘት ነበረች፡፡ በተከታታይም፣ የአህዛብ መጉረፍ ለሁሉም ዓይነት ነገረ-መለኮታዊና ተግባራዊ ችግሮች ምንጭ ሆነ፡፡ ለምሳሌ፣ እነዚህ አህዛቦች የአይሁድን ወግ መጠበቅ ይገባቸዋል? የብሉይኪዳን አማኞች ለማድረግ ይገደዱ እንደነበረው እነርሱም የሙሴን ህግጋት ሊጠብቁ ይገደዳሉ? እነዚህን የመሳሰሉ ጥያቄዎች የሐሰት መምህራን በገላትያ እንዲነሱ ዕድል ሰጣቸው፡፡ እነዚህም የአይሁድ መምህራን እንዲገረዙ ግድ በማለት በቤተክርስቲያን ውስጥ ወደሚገኙ አህዛብ የሚቀርቡበትን የራሳቸውን መንገድ ይዘው መጡ፡፡

ጳውሎስ በመጀመሪያ ሚሲዮናዊ ጉዞው አህዛብ አማኞችን አልገረዘም፣ እርሱ ዘወር ሲል ግን የሐሰት መምህራኑ ተቃራኒውን ያስተምሩ ነበር፡፡ እግዚአብሔር ግዝረትን ለእስራኤል እንደደነገገ ጳውሎስ ያውቃል ደግሞም ከመገረዝ ጋር ጠብ የለበትም፡፡ ሆኖም ግን በገላትያ አህዛብ እንዲገረዙ የመገደዳቸው ነገር ጳውሎስ በቸልታ የሚያልፈው አልሆነም፡፡ ጉዳዩ ከክርስትናው ወንጌል ልቡና የሚገነጠሉበትን ብርቱ አደጋ የደቀነ ነበር፡፡

የአህዛብ ክርስቲያኖች እንዲገረዙ የመገደዳቸው ነገር ስለ ክርስትና እምነት ያለውን ግንዛቤ በእጅጉ እንደሚያዛባ ጳውሎስ ያነገበውን አቋም በሦስት መንገዶች እንዳስሳለን፡፡ በመጀመሪያ፣ ለድነት የክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ብቁ መሆኑን ይክዳል፤ ሁለተኛ፣ በሥጋ ጉልበት ላይ ተገቢ ባልሆነ መንገድ መታመንን ያሳያል፤ ሦስተኛ ደግሞ፣ በገላትያ አብያተክርስቲያናት ውስጥ መከፋፈልን ያመጣል፡፡ አስቀድመን የክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ለድነት ብቁ መሆኑን የሐሰት መምህራን የካዱበትን መንገድ እንመልከት፡፡

ከገላትያ መጽሐፍ በመነሳት በገላትያ የሚኖሩ የሐሰት መምህራን ግዝረትን የሚመለከቱት አማኞች እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ኑሮ እንዲኖሩ እንደሚያስችላቸው እንደ ደም መስዋዕት እንደሆነ እንገምታለን፡፡ በእነርሱ አመለካከት፣ ክርስቲያኖች በክርስቶስ የማዳን ሥራ ላይ ግርዛትን ሊጨምሩ ይገባል፡፡ እንደ ጳውሎስ አመለካከት ግን ይህ እምነት የክርስቶስን ሞት እውነተኛ ትርጉምና ዋጋ የሚያቃልል ነው፡፡ ጳውሎስ በገላትያ 5፡2 እንዲህ የጻፈው በዚህ ምክንያት ነው፡

> ***እነሆ፥ እኔ ጳውሎስ እላችኋለሁ፡- ብትገረዙ ክርስቶስ ምንም አይጠቅማችሁም። (ገላትያ ፡2)***

የክርስቶስን የማዳን ሥራ ብቁነት ከማቃለል በተጨማሪም፣ በገላትያ የነበሩት የሐሰት መምህራን አማኞች ድነታቸውን ፍፁም ለማድረግ በሥጋ መታመን እንዳለባቸው በማስተማር ጳውሎስ ያስተምር የነበረውን ወንጌል ይገዳደሩ ነበር፡፡ ጳውሎስም በገላትያ 3፡3 ውስጥ ችግሩን በጽኑ በማንሳት በግርምት (በሽሙጥ ዓይነት) እንዲህ ሲል ይጠይቃል፡

> ***እንዲህን የማታስተውሉ ናችሁ? በመንፈስ ጀምራችሁ አሁን በሥጋ ትፈጽማላችሁን? (ገላትያ 3፡3)***

"ሰብዓዊ ጥረት" የተሰኘውን ቃል ለማመልከት የተጠቀመው ቃል በግሪኩ *sarx* (sa,rx) ሲሆን፣ በተለምዶ "ሥጋ" ተብሎ ይተረጎማል፡፡ ጳውሎስም ሥጋ ወይም *sarx* የተሰኘውን ቃል የተጠቀመው ሰብዓዊ ኃይልን ለማመልከት ሲሆን በተለይም ኃጢአተኛ የሆነውን ሰብዓዊ መንገድ ለማሳየት ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ ስፍራ ያለው ሃሳብ "ሰብዓዊ ጥረት" የሚለውን ያመለክታል፡፡

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

ጳውሎስ ለመጀመሪያ ጊዜ በገላትያ ሲያገለግል፣ ስብከቱ አስደናቂ በሆነው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተግባራዊ መገለጥ የታጀበ ነበር፡፡ የገላትያ ሰዎችም የክርስትና ሕይወታቸውን የጀመሩት በመንፈስ ኃይል ነበር፡፡ አሁን ግን፣ ወደ መገረዝ በመመለስ፣ እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኝ ሕይወት ለመመላለስ በራሳቸው ሰብዓዊ ችሎታ ላይ መደገፍ ጀመሩ፡፡ በሚያሳዝን መንገድ፣ ይህ በሰብዓዊ ችሎታ ላይ የመደገፋቸው ነገር ለአቅመ ደካማነትና ለውድቀት በሚዳረጉበት እርግማን ውስጥ ጣላቸው፡፡

የክርስቶስን ሥራ ክቡር ዋጋና የመንፈስ ቅዱስን ወሳኝነት ከመካድም በተጨማሪ፣ የሐሰት መምህራኑ በገላትያ ቤተክርስቲያን ውስጥ መከፋፈልን በመፍጠራቸው ጳውሎስ በእጅጉ ተቸግሮ ነበር፡፡ ይህንንም በገላትያ 6፡15-16 እንዲህ አስፍሮታል፡

> ***በክርስቶስ ኢየሱስ አዲስ ፍጥረት መሆን ይጠቅማል እንጂ መገረዝ ቢሆን ወይም አለመገረዝ አይጠቅምምና።***
> ***በዚህም ሥርዓት በሚመላለሱ ሁሉ ላይ በእግዚአብሔር እስራኤልም ላይ ሰላምና ምሕረት ይሁን። (ገላትያ 6፡15-16)***

በአይሁድና በአህዛብ መካከል የነበረው መለያየት በክርስቶስ ተወግዷል፡፡

በገላትያ አብያተክርስቲያናት መካከል የነበረው መለያየት ጳውሎስን በእጅጉ አውኮታል፡፡ በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል የእርስ በርስ ጠብና መለያየት ክርስቶስ ከሠራው ሥራ ጋር ፈፅሞ የሚቃረን ሲሆን፣ ቤተክርስቲያንም ልትተጋበት ከሚገባው ተገቢ አካሄድ ጋር ፈፅሞ የማይጣጣም ነው፡፡ የሐሰት መምህራኑ ግን በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል ሙሉ ተቀባይነትን ለማግኘት መገረዝ ወሳኝ ነው የሚል የብሉይ ኪዳን ህግ ይከተሉ ነበር፡፡ በቤተክርስቲያን ውስጥ ለሚገኙ ለአብዛኞቹ ሰዎች በተለይም ለአይሁድ ክርስቲያኖች መገረዝን ያልተቀበለ የትኛውም ሰው ራሱን እንደ ሁለተኛ ዜጋ ቆጥሯል የሚለው አስተሳሰብ የተለመደ ነበር፡፡ ስለዚህ በተገረዙትና ባልተገረዙት መካከል መለያየቱ ቢፈጠር አያስገርምም፡፡

የሐሰት መምህራኑ በገላትያ አብያተክርስቲያናት መካከል እጅግ በጣም አደገኛ ችግሮችን እንደፈጠሩ እንመለከታለን፡፡ እነዚህ የሐሰት መምህራን እያደረጉ ያለውን ነገር ከሰማ በኋላ፣ ጳውሎስ ዝም ብሎ አልተቀመጠም፡፡ የገላትያ ሰዎች መንፈሳዊ ልጆቹ ነበሩ፤ በእርሱ የተወደዱ ነበሩ፡፡ ስለዚህ የአይሁድንም ሆነ የአህዛብ አማኞችን ከእነዚህ የሐሠት መምህራን አፍራሽ አመለካከቶች ለመታደግ መልእክቱን ጻፈላቸው፡፡

ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች የጻፈውን መልእክት ዳራ አንዳንድ ወሳኝ ገፅታዎች ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ የመልእክቱን አወቃቀርና ይዘት በበለጠ ጥልቀት ለመመልከት እንዘጋጃለን፡፡ ጳውሎስ ለገላትያ አብያተክርስቲያናት ምን ጻፈ? ለችግሮቻቸው ምላሽ የሰጠው እንዴት ነበር? እያንዳንዳቸውን ክፍሎች ጠቅለል አድርገን በመመልከት የገላትያን መጽሐፍ በመጠኑ እንዳስሳለን፡፡

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

# 3. ይዘት

የገላትያ መልእክት በስድስት ዋና ክፍሎች ይከፈላል፡፡ በመጀመሪያ፣ በ1፡1-5 ቅድመ ጽሑፍ፤ ሁለተኛ፣ በ1፡6-10 በገላትያ ስላለው ችግር መንደርደሪያ፤ ሦስተኛ፣ በ1፡11-2፡21 የተለያዩ ታሪካዊ ዘገባዎች፤ አራተኛ፣ በ3፡1-4፡31 ጽድቅ በእምነት ለተሰኘው አስተምህሮ ተከታታይ ማስረጃዎች፤ አምስተኛ፣ በ5፡1-6፡10 ጥቂት ተግባራዊ ማሳሰቢያዎች እና በመጨረሻ፣ በ6፡11-18 ድኅረ ጽሑፍ ናቸው፡፡

## ቅድመ ጽሑፍ/ድኅረ-ጽሑፍ

የገላትያ ቅድመ ጽሑፍ አጭርና ቀጥተኛ ነው፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስን እንደ ጸሐፊ፣ የገላትያ አብያተክርስቲያናትን ደግሞ እንደ ተቀባዮች ያስተዋውቃል፡፡ ድኅረ ጽሁፉም እንዲሁ አጭር ሲሆን፣ ጳውሎስ ለአብያተክርስቲያናቱ በሚያስተላልፈው ቡራኬ መልእክቱን ይደመድማል፡፡ በዚህ ደብዳቤ ጳውሎስ ያነሳቸው ወሳኝ አስተሳሰቦችንም ያሰምርባቸዋል፡፡

## የችግሩ መንደርደሪያ

በሁለተኛው ክፍል፣ 1፡6-10፣ "የችግሩ መንደርደሪያ" ብለን በሰየምነው ክፍል፣ ጳውሎስ ወዲያውኑ በገላትያ የነበረውን የስህተት አስተምህሮ ችግር ጥቃት ይሰነዝርበታል፡፡ መደነቁን ይገልጽና የሐሰት መምህራኑን መከተል ምን ያህል አደገኛ እንደሆነ እንዲያስተውሉ አንባቢዎቹን ያስጠነቅቃል፡፡ ምንም በማያጠራጥር መንገድ፣ የእርሱን አስተምህሮ መቃወም ሐሰተኛ ወንጌል መቀበል መሆኑን ጳውሎስ ያሳያል፡፡ በ1፡8 ውስጥ በሐሰት መምህራን ላይ የሰነዘረውን ከባድ እርግማን እናድምጥ፡

> ***ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ፥ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ፥ የተረገመ ይሁን። (ገላትያ 1፡8)***

የሐሰት መምህራኑን አስተምህሮ መከተል ማለት የክርስቶስን ወንጌል መቃወም፣ እንዲያውም ድነትን ራሱን ማቃለል ማለት ነው፡፡ ይህ የመልእክቱ ክፍል በገላትያ የነበሩት ችግሮች እስከዚህ አይደሉም ሊባሉ እንደማይችሉ ግልጽ አድርጎታል፡፡ የገላትያ ሰዎች ዕጣ ፈንታ አደጋ ውስጥ ወድቋል፡፡

## ታሪካዊ ዘገባዎች

በ1፡11-2፡21 የሚገኘው፣ ሦስተኛው ክፍል፣ ሰፋ ያለ ነው፡፡ ጳውሎስ ሥልጣኑን ያረጋገጠባቸውን የተለያዩ ታሪካዊ ዘገባዎች ይዟል፡፡ በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ የተለያዩ ታሪካዊ ክንውኖች ፊት ለፊት ይመጣሉ፣ እነርሱም፣ የጳውሎስ ጥሪና ስልጣና 1፡11-17፤ ጳውሎስ በኢየሩሳሌም ከሚገኙ መሪዎች ጋር መገናኘቱ በ2፡1-10 እና ጳውሎስ በሶርያዋ አንጾኪያ ከጴጥሮስ ጋር መጋጨቱ በ2፡11-21 ናቸው፡፡

### ጥሪና ስልጠና

የጳውሎስ ጥሪና ስልጠና የአህዛብን መገረዝ ለመቃወም የሚያስችል ሥልጣን ጳውሎስ እንዴት እንደነበረው ያብራራል፡፡ ጳውሎስ ምን ያህ የእስራኤልን ትውፊት እንደሚወድድ መግለጫ በመስጠት ይጀምራል፡፡ በገላትያ 1፡13-14 የተናገረውን እናድምጥ፡

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

*በአይሁድ ሥርዓት በፊት እንዴት እንደ ኖርሁ ሰምታችኋልና፤ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ያለ ልክ አሳድድና አጠፋ ነበር፥*
*ለአባቶችም ወግ ከመጠን ይልቅ እየቀናሁ በወገኔ ዘንድ በዘመኔ ካሉት ብዙዎችን በአይሁድ ሥርዓት እበልጥ ነበር። (ገላትያ 1፡13-14)*

ነገር ግን ጳውሎስ የእርሱ አስተሳሰብ እንዴት እንደተለወጠም ያብራራል፡፡ አስቀድሞ ለአይሁድ ወግ ቀናዒ ቢሆንም፣ በገላትያ በኩል ሲያልፍ ግን፣ አህዛብ እንዲገረዙ ግድ አላላቸውም፡፡ ለመሆኑ ለእስራኤል ወግ ያንን ያህል የተሰጠ ከነበረ ይህንን እንዴት ሊያደርግ ቻለ? በገላትያ 1፡15-18 ጳውሎስ የሰጠውን ምስክርነት አድምጡ፡

*ነገር ግን በእናቴ ማኅፀን ሳለሁ የለየኝ በጸጋውም የጠራኝ እግዚአብሔር በአሕዛብ መካከል ስለ እርሱ ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ልጁን በእኔ ሁኔታ ሊገልጥ በወደደ ጊዜ፥ ወዲያው ከሥጋና ከደም ጋር አልተማከርሁም፥*
*ከእኔም በፊት ሐዋርያት ወደ ነበሩት ወደ ኢየሩሳሌም አልወጣሁም፥ ነገር ግን ወደ ዓረብ አገር ሄድሁ እንደ ገናም ወደ ደማስቆ ተመለስሁ።*
*ከዚህ ወዲያ ከሦስት ዓመት በኋላ ኬፋን ልጠይቅ ወደ ኢየሩሳሌም ወጥቼ ከእርሱ ጋር አሥራ አምስት ቀን ሰነበትሁ፤ (ገላትያ 1፡15-18)*

ጳውሎስ ስለ ወንጌልና ስለ ክርስቲያናዊ አስተምህሮ በቀጥታ ከኢየሱስ ለመማር ለሦስት ዓመታት ያህል በዓረቢያ አሳልፏል፡፡ አህዛብ እንዲገረዙ ማስገድ አያስፈልግም የሚለውን አቋም የያዘው በተፈጥሯዊ አመክንዮ ወይም በግል ምርጫው አልነበረም፡፡ ጌታ ኢየሱስ፣ ራሱ፣ የእርሱን አዳዲስ አስተሳሰቦች ለጳውሎስ አስተማረው፡፡ በዚህ ጉዳይ ከጳውሎስ ጋር አለመስማማት ማለት ከክርስቶስ ከራሱ ጋር አለመስማማት ማለት ነው፡፡

## ከመሪዎች ጋር መገናኘት

በገላትያ ውስጥ የምናገኘው ሁለተኛው ታሪካዊ ዘገባ የሚገኘው በ2፡1-10 ሲሆን፣ ጳውሎስ ከኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን መሪዎች ጋር ያደረገውን ስብሰባ የሚዘግብ ነው፡፡ በቀላሉ ለማስቀመጥ፣ ከጴጥሮስ ጋር በግል ከተገናኙ ከዐሥራ አራት ዓመታት በኋላ፣ ከኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን መሪዎች ጋር ጳውሎስ ተገናኝቶ ነበር፡፡ በዚህም ስብሰባ ለአህዛብ ወንጌልን ለመስበክ እርሱ የመረጠውን አቀራረብ ተቀብለውታል፡፡ በገላትያ 2፡1-9 ጳውሎስ የዘገበውን አድምጡ፡

*… ወደ ኢየሩሳሌም ሁለተኛ ወጣሁ፤*
*እንደ ተገለጠልኝም ወጣሁ፤ ምናልባትም በከንቱ እንዳልሮጥ ወይም በከንቱ ሮጬ እንዳልሆን በአሕዛብ መካከል የምሰብከውን ወንጌል አስታወቅኋቸው፤ …*
*ለእኔ ሳልተገረዙት የሆነው ወንጌል አደራ እንደ ተሰጠኝ አዩ፤ …*
*ደግሞ የተሰጠኝን ጸጋ አውቀው፥ አዕማድ መስለው የሚታዩ ያዕቆብና ኬፋ ዮሐንስም እኛ ወደ አሕዛብ እነርሱም ወደ ተገረዙት ይሄዱ ዘንድ ለእኔና ለበርናባስ ቀኝ እጃቸውን ሰጡን፤ (ገላትያ 2፡1-9)*

ጳውሎስ ይህንን ታሪክ ከገላትያ ሰዎች ጋር ያዛምደዋል፣ ያንንም ያደረገው በአህዛብ መካከል እርሱ እየሠራ ያለው ሥራ በኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን ያሉ መሪዎች ከሚያስተምሩት ሥልጣን ያለው ትምህርት ጋር እንደማይጣረስ

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

እንዲያዩ ነው፡፡ እንዲያውም፣ ጳውሎስ ለአህዛቡ ዓለም ወንጌልን እንዲያደርስ እግዚአብሔር ልዩ አደራ እንደሰጠው የተቀሩት ሐዋርያት ተረድተዋል፡፡ ስለዚህ፣ ጳውሎስ ስለ አህዛብ መገረዝ የቀረበውን ጥያቄ እርሱ ያምንበት በነበረው መንገድ የመመለስ ሙሉ መብት ነበረው፡፡

## ከጴጥሮስ ጋር የገጠመው ግጭት

የጳውሎስ ሦስተኛው ታሪካዊ ዘገባ የሚገኘው በ2፡11-21 ውስጥ ሲሆን፣ በሶርያዋ አንፆኪያ ከጴጥሮስ ጋር ስለ ገጠመው ግጭት ያብራራል፡፡ ጴጥሮስ ወደ መጀመሪያ አካባቢ፣ ካልተገረዙ አማኞች ጋር በነፃነት ይተባበር ነበር፡፡ ሆኖም ቆየት ብሎ ግን፣ በኢየሩሳሌም ከሚኖሩ ወግ አጥባቂ አይሁድ አማኞች ተቃውሞ እንዳይገጥመው ብሎ ይፈራ ነበር፡፡ ስለዚህም ራሱን ካልተገረዙ አማኞች አገለለ፡፡

ጴጥሮስ በልቡ ምንም ይመን ምን፣ በተግባሩ ግን ያልተገረዙ አማኞች ከአይሁድ አማኞች ያንሳሉ ከሚለው የተሳሳተ እምነት ጋር ተስማምቶ ነበር፡፡ ጳውሎስ ይህንን ሲያውቅ፣ ጴጥሮስን ፊት ለፊት በመጋፈጥ እርሱም ሆነ ጴጥሮስ ስላመኑበት ወንጌል አሳሰበው፡፡ ጳውሎስ ለጴጥሮስ በዚያን ወቅት የተናገረውን ገላትያ 2፡15-16 ዘግቦታል፡፡

> ***እኛ በፍጥረት አይሁድ ነን ኃጢአተኞችም የሆኑ አሕዛብ አይደለንም፤ ነገር ግን ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንዲጸድቅ እንጂ በሕግ ሥራ እንዳይሆን አውቀን፥ ሥጋን የለበሰ ሁሉ በሕግ ሥራ ስለማይጸድቅ፥ እኛ ራሳችን በሕግ ሥራ ሳይሆን በክርስቶስ እምነት እንጸድቅ ዘንድ በክርስቶስ ኢየሱስ አምነናል። (ገላትያ 2፡15-16)***

ጳውሎስ ከጴጥሮስ ጋር ስለነበረው ግጭት የዘገበው ጴጥሮስ እንኳን ሳይቀር በዚህ ጉዳይ ለጳውሎስ ሥልጣናዊ እርምት ራሱን አስገዝቶ እንደነበር ለማመልከት ነው፡፡ የጳውሎስ ሥልጣን፣ አዕማድ ሐዋርያ የነበረውን ጴጥሮስን እንኳን ሳይቀር የማረም ብቃት ከነበረው፣ በገላትያ የነበሩ የሐሰት መምህራንን በእርግጠኝነት የማረም ብቃት አለው፡፡

በእነዚህ ሦስት ዘገባዎች ማለትም፣ ጥሪና ስልጠናው፣ ከኢየሩሳሌም ባለሥልጣናት ጋር መገናኘቱ እና ጴጥሮስን ፊት ለፊት መጋፈጡ፣ በገላትያ የነበሩትን የሐሰት መምህራን ለማረምና ወንጌሉን ለመመከት ጳውሎስ ጠንካራ መሠረት ጥሎባቸዋል፡፡

# ነገረ-መለኮታዊ ማረጋገጫዎች

ጳውሎስ የዘረዘርናቸውን ታሪካዊ ዘገባዎች ካቀረበ በኋላ፣ በ 3፡1-4፡31 ወደሚገኘው አራተኛው ክፍል ይሸጋገራል፡፡ በዚያም ውስጥ ጽድቅ በእምነት ለሚለው አስተምህሮው ቀጥተኛ የሆኑ ነገረ-መለኮታዊ መከራከሪያዎችን ያቀርባል፡፡ ይህም በአራት ክፍሎች ይከፈላል፣ ያም በገላትያ ሰዎች ልምምድና በአብርሃም ሕይወት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዘገባ መካከል ያለውን በማነፃፀር የቀረበ ነው፡፡ በመጀመሪያ፣ ጳውሎስ የገላትያ ሰዎች ቀደም ብሎ የነበራቸውን ልምምድ ያሳስባቸዋል፡፡ ሁለተኛ፣ ስለ አብርሃም ድነት በእምነት ብሉይ ኪዳን ወዳሰፈረው ዘገባ ይሸጋገራል፡፡ ሦስተኛ፣ የገላትያ አማኞች አሁን ስላሉበት ልምምድ ያነሳል፡፡ አራተኛ ደግሞ፣ ስለ አብርሃም ሚስቶችና ልጆች የተጻፈውን ታሪክ ይጠቅሳል፡፡

## የመጀመሪያ ልምምድ

የገላትያ ሰዎች በክርስትና እምነት ውስጥ በነበራቸው የመጀመሪያ ልምምድ ላይ አተኩሮ ጳውሎስ የተናገረበትንና በ 3፡1-5 የሚገኘውን ክፍል በጥቂቱ እንመልከት፡፡ በገላትያ 3፡2-5 እንዲህ ጽፏል፡

***ይህን ብቻ ከእናንተ እንድማር እወዳለሁ፤ በሕግ ሥራ ወይም ከእምነት ጋር በሆነ መስማት መንፈስን ተቀበላችሁን?***
***እንዲህን የማታስተውሉ ናችሁ? በመንፈስ ጀምራችሁ አሁን በሥጋ ትፈጽማላችሁን?***
***በውኑ ከንቱ እንደ ሆነስ እንደዚህ ያለ መከራ በከንቱ ተቀበላችሁን?***
***እንግዲህ መንፈስን የሚሰጣችሁ በእናንተም ዘንድ ተአምራት የሚያደርግ፥ በሕግ ሥራ ነውን ወይስ ከእምነት ጋር በሆነ መስማት ነው? (ገላትያ 3፡2-5)***

ተከታታይ አሳማኝ ጥያቄዎችን በመጠየቅ፣ ጳውሎስ የመጀመሪያውን ሚሲዮናዊ ጉዞ ያጣቅሳል፡፡ የሐዋርያት ሥራ 13-14 እንደሚነግረን፣ ጳውሎስ ለመጀመሪያ ጊዜ ከእነርሱ ጋር በነበረበት ወቅት የገላትያ ሰዎች ከመንፈስ ቅዱስ አስደናቂ በረከቶችን ተቀብለው ነበር፡፡ እነዚህ የመንፈስ ቅዱስ በረከቶች የመጡት እነርሱ የእግዚአብሔርን ህግጋት ስለጠበቁ እንዳልነበረ የገላትያ ሰዎችም እርሱም ያውቃሉ፡፡ እግዚአብሔር እነዚያን ስጦታዎች በነፃ የሰጣቸው በወንጌል በማመናቸው ብቻ ነበር፡፡ ከዚህ ልምምድ በመነሳት፣ የገላትያ ሰዎች እየቆዩ በሄዱ ቁጥር ይበልት ሊያውቁ ይገባ ነበር እንጂ፣ የኋላ ኋላ የእግዚአብሔርን በረከቶች ህግን በመጠበቅ ለማግኘት ማሰብ አልነበረባቸውም፡፡

## የአብርሃም እምነት

የቀደመ ክርስቲያናዊ ልምምዳቸውን ከዳሰሰ በኋላ፣ ጳውሎስ ወደ አብርሃም በእምነት የመጽደቅ ምሳሌ ይሸጋገራል፡፡ በ 3፡6 -4፡11 ድረስ እግዚአብሔር አብርሃምን የባረከው በእምነት እንጂ፣ አብርሃም የእግዚአብሔርን ህግ በመጠበቁ አይደለም በማለት መከራከሪያውን ያቀርባል፡፡ አብርሃም የድነትን በረከቶች ያገኘው ከንቱ በሆኑ ሰብዓዊ ጥረቶች አማካይነት አይደለም፡፡ በዚህ ክፍል ጳውሎ ያቀረበው ሙግት ወሰብሰብ ያለ ነው፣ እኛ ግን በአራት ደረጃዎች ሰብስብ አድርገን እናቀርበዋለን፡፡

አንደኛ፣ አብርሃም የጸደቀው ልጅ እንደሚሰጠው እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ በማመን እንደሆነ ጳውሎስ ያመለክታል፡፡ በ 3፡6-7 ውስጥ ጳውሎስ ዘፍጥረት 15፡6 ን እንዲህ ብሎ ያጣቅሳል፡

***እንዲሁ አብርሃም በእግዚአብሔር አመነና ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት።***
***እንኪያስ ከእምነት የሆኑት እነዚህ የአብርሃም ልጆች እንደ ሆኑ እወቁ። (ገላትያ 3፡6-7)***

እንደ ጳውሎስ አመለካከት፣ አብርሃም የጸደቀው በእግዚአብሔር ቃል በማመኑ እንጂ ከዓመታት በኋላ በፈፀመው የመገረዝ ሥርዓት ምክንያት እንዳልሆነ ዘፍጥረት 15፡6 በግልጽ አስቀምጦታል፡፡ ይህንን መሠረት በማድረግ፣ እውነተኛ የአብርሃም ልጆች የሆኑት ለድነት እግዚአብሔር በሰጠው ተስፋ የማመንን ምሳሌነት የሚከተሉ ናቸው በማለት ጳውሎስ ድምዳሜውን ያቀርባል፡፡ ድነት በእምነት የሚገኝ በረከት እንጂ በመገረዝ የሚገኝ አይደለም፡፡

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

ሁለተኛ፣ ያልተገረዙ አህዛብን አስመልክቶ የተለያዩ ክርክሮች ተነስተው ስለነበር፣ የድነት በረከት በእርሱ አማካይነት ወደ አህዛብ ሁሉ እንደሚደርስ እግዚአብሔር ለአብርሃም ነግሮት እንደነበር ወደ ማመልከቱ ጳውሎስ ይሸጋገራል፡፡ በገላትያ 3፡8-9 ጳውሎስ ዘፍጥረት 12፡3 እንዲህ ያጣቅሰዋል፡

*መጽሐፍም እግዚአብሔር አሕዛብን በእምነት እንዲያጸድቅ አስቀድሞ አይቶ፦ በአንተ አሕዛብ ሁሉ ይባረካሉ ብሎ ወንጌልን ለአብርሃም አስቀድሞ ሰበከ።*
*እንደዚህ ከእምነት የሆኑት ካመነው ከአብርሃም ጋር ይባረካሉ። (ገላትያ 3፡8-9)*

በመላው ዓለም የሚገኙ አህዛብ የእግዚአብሔርን በረከት የሚቀበሉበትን ዘመን እግዚአብሔር አስቀድሞ ተስፋ ሰጥቷል ብሎ ለማስተማር ዘፍጥረት 12፡3 ጳውሎስ ይጠቅሳል፡፡ ይህ በረከት አስቀድሞ ወደ አብርሃም በመጣበት መንገድ፣ በእምነት ወደ ዓለም ሁሉ ይመጣል፡፡

ሦስተኛ፣ በመገረዝ ወቅት የሚከናወነው ሥጋን የመቆራረጥ ተግባር ራስን ለእርግማን አሳልፎ የመስጠት ተምሳሌት እንጂ ጽድቅ የማግኛ መንገድ አለመሆኑን የገላትያ ሰዎች እንዲረዱ ጳውሎስ ይፈልጋል፡፡ መገረዝ ማለት "ቃል ኪዳኑን በታማኝነት ባልጠብቅ ከሕያዋን ምድር ተቆርጬ ልቅር" ማለት ነው፡፡ ክርስቶስ የመጣው ማንም ሰው በዚያ ልኬት መሠረት ሊኖር ስላልቻለ ነው፡፡ ጳውሎስ በገላትያ 3፡13 እንዳስቀመጠው፡

*በእንጨት የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎአልና ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ዋጀን፤ (ገላትያ 3፡13)*

በአይሁዳውያን ግንዛቤ መሠረት፣ በመስቀል ላይ መንጠልጠል እጅግ አሳፋሪና የተረገመ አሟሟት ነው፡፡ ክርስቶስ ይህንን የኃጢአት አሰቃቂ እርግማን ወሰደ፡፡ ክርስቶስ በእነርሱ ምትክ ሆኖ እርግማኑን ስለወሰደላቸው ሙሉ በሙሉ በእምነት ብቻ፣ ለቃል ኪዳኑ ታማኝ የመሆን በረከቶች የእነርሱ እንደሆኑ የገላትያ ሰዎች ሊረዱ ያስፈልጋል፡፡

በአራተኛ ደረጃ፣ ጳውሎስ የሐሰት መምህራኑን ተቃውሞ ራቁቱን የሚያስቀረውየሙሴ ሕግ የአብርሃምን ተምሳሌት ሊቀለብሰው አይችልም ብሎ በመሟገት ነው፡፡ በገላትያ 3፡17-19 እንዲህ አስቀምጦታል፡

*ይህንም እላለሁ፤ ከአራት መቶ ሠላሳ ዓመት በኋላ የተሰጠው ሕግ አስቀድሞ በእግዚአብሔር የተረጋገጠውን ኪዳን የተስፋውን ቃል እስኪሽር ድረስ አያፈርስም።*
*ርስቱ በሕግ ቢሆንስ እንግዲያስ በተስፋ ቃል አይሆንም፤ በተስፋ ቃል ግን እግዚአብሔር ለአብርሃም ሰጥቶአል።*
*እንግዲህ ሕግ ምንድር ነው? ተስፋው የተሰጠው ዘር እስኪመጣ ድረስ በመካከለኛ እጅ በመላእክት በኩል ስለ ሕግ መተላለፍ ተጨመረ። (ገላትያ 3፡17-19)*

ከጳውሎስ አመለካከት አንፃር፣ ሕጉ የተሰጠው በገላትያ የሚኖሩ የሐሰት መምህራን እንደሚያውጁት የእግዚአብሔርን በረከቶች በሥራ እንዲያገኙ ለማስቻል አይደለም፡፡ የሙሴ ሕግ የተጨመረው የእስራኤልን ኃጢአት አፍጥጦ ለማውጣትና ለክርስቶስ ለማዘጋጀት ነው፡፡

በአምስተኛ ደረጃ፣ የእግዚአብሔር በረከቶች ሊመጡ የሚችሉት የአብርሃም ልዩ ልጅ ከሆነው፣ ከክርስቶስ ጋር ግንኙነት ወዳላቸው ብቻ እንደሆነ ጳውሎስ ያውጃል፡፡ በገላትያ 3፡16፣29 ጳውሎስ እንዲህ ጽፏል፡

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

***ለአብርሃምና ለዘሩም የተሰፋው ቃል ተነገረ። ስለ ብዙዎች እንደሚነገር፦ ለዘሮቹም አይልም፤ ስለ አንድ እንደሚነገር ግን፦ ለዘርህም ይላል፥ እርሱም ክርስቶስ። ... እናንተም የክርስቶስ ከሆናችሁ እንኪያስ የአብርሃም ዘር እንደ ተሰፋውም ቃል ወራሾች ናችሁ። (ገላትያ 3፡16፣29)***

ጳውሎስ የዘፍጥረትን ዘገባ በሚያነብበበት ወቅት፣ በ22፡18 ውስጥ ዘር ጠብሎ የተተረጎመው ቃል በዕብራይስጡ *zera* የተሰኘው ቃል የነጠላ ቁጥር እንጂ የብዙ ቁጥር አይደለም፡፡ የአብርሃም ውርስ ለአብርሃም ልጆች በጠቅላላ አልተሰጠም፣ በመጀመሪያ የተሰጠው ከእርሱ ለተወለዱት ሁሉ ወኪል ለሚሆነው ለልጁ ነው፡፡ እናም ከክርስቶስ በተገኘው የራእይ ብርሃን መሰረት፣ ክርስቶስ ታላቁ የአብርሃም ዘር ማለትም በዘመናት ሁሉ ለሚመጣው የእግዚአብሔር ህዝብ የመጨረሻው ወኪል ነው፡፡ ለአብርሃም የተሰጡትን ተስፋዎች ሁሉ የወረሰ ታላቁ ዘር ክርስቶስ ነው እናም ግለሰቦች የዚህ ውርስ ተካፋይ የሚሆኑት የእርሱ ከሆኑ ብቻ ነው፡፡

በእነዚህ መንገዶች፣ ጽድቅ ሊገኝ የሚችለው የአብርሃምን ተምሳሊት ለሚከተሉ እና የእግዚአብሔርን በረከት በአብርሃም ልጅ አማካይነት ለሚቀበሉ ሲሆን፤ ይህም ድነት የሚገኘው የእግዚአብሔርን ተስፋዎች በእምነት በመቀበል እንጂ ህግን በመፈፀም በሥራ አይደለም፡፡

## አሁን ያሉበት ልምምድ

ጳውሎስ የገላትያ ሰዎች አስቀድሞ የነበራቸውን የድነት ልምምድ እና የአብርሃምን እምነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዘገባ ካቀረበ በኋላ፣ በገላትያ 4፡12-20 የገላትያ ሰዎች አሁን ያሉበትን ልምምድ ያነሳል፡፡ በ 4፡15-16 ምን እንደጻፈ እናድምጥ፡

***እንግዲህ ደስ ማሰኘታችሁ ወዴት አለ? ቢቻልስ ዓይኖቻችሁን አውጥታችሁ በሰጣችሁኝ ብዬ እመሰክርላችኋለሁ።***
***እንኪያስ እውነቱን ስለ ነገርኋችሁ ጠላት ሆንሁባችሁን? (ገላትያ 4፡15-16)***

ጳውሎስ በዚህ ስፍራ ለገላትያ ሰዎች መንፈሳዊ ጤናማነት የነበረውን ጽኑ ናፍቆት ገልጧል፤ ያሉበትን አሳዛኝ መንፈሳዊ ሁኔታ እንዲገነዘቡ ፈልጓል፡፡ የገላትያ ሰዎች ከወንጌል ዘወር ሲሉ፣ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ የሆነውንና ሊያጣጥሙት የሚገባውን ደስታቸውን አጥተዋል፡፡ ይህ ኪሳራ በራሱ የጳውሎስ ተቃዋሚዎች የሚያስተምሩት ትምህርት ችግር እንዳለበት ለገላትያ ሰዎች ማስጠንቀቂያ ሊሆን ይገባው ነበር፡፡

## የአብርሃም ሚስቶችና ወንዶች ልጆች

ጳውሎስ ከሐሰት መምህራኑ ጋር ሙግት የገጠመበት አራተኛው መንገድ በገላትያ 4፡21-31 በተመዘገበውና በአብርሃም ሚስቶችና ወንዶች ልጆች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዘገባ ላይ ማትኮር ነው፡፡ በዘፍጥረት ምእራፍ 15 ውስጥ ከሚስቱ ከሳራ ወራሽ እንደሚሰጠው እግዚአብሔር ለአብርሃም ተስፋ ይሰጠዋል፡፡ ሳራ ግን መካንና ልጅ የመውለጃ ዕድሜዋ ያለፈባት ነበረች፣ ስለዚህ ከእርሷ ዘርን ለማግኘት አብርሃም በእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች መታመን ያስፈልገው ነበር፡፡ እግዚአብሔር ቃሉን እንደሚጠብቅ በመታመናቸው፣ ሳራ ወንድ ልጅ፣ ይስሐቅን ወለደች፡፡ የሳራ ልጅ ይስሐቅ የተስፋ ልጅ ነበር እርሱም የአብርሃም ዘርና ለሚያምኑ ሁሉ ወኪላቸው ሆኖ ተቆጠረ፡፡

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

ሆኖም፣ ዘፍጥረት 16 እንደሚነግረን፣ ይስሐቅ ከመወለዱ በፊት፣ እግዚአብሔር ተስፋ የገባውን ወንድ ልጅ ይሰጠኛል ብሎ የሚጠብቅበት ዕድሜ አለፈ ስለዚህም ታከተው፡፡ ስለዚህም፣ ልጅ ለማግኘት ወደ አጋር ባሪያ ገባ፡፡ ይህንንም በማድረጉ፣ አብርሃም እግዚአብሔር የገባለትን ተስፋ በሰው ሥጋዊ ጥረት ለመፈፀም ፈለገ፡፡ አጋርም፣ እስማኤል የተባለ ልጅ ወለደችለት፣ እስማኤል ግን የሥጋ ልጅ ነበር፡፡ እግዚአብሔርም የአብርሃም ዘር አድርጎ አልቆጠረውም እናም መዳንን በሥጋዊ መንገድ ለማግኘት ለሚሞክሩ ሁሉ ወኪላቸው ሆነ፡፡ ጳውሎስም በአብርሃም ሚስቶችና ወንዶች ልጆች ማካከል ያለውን ልዩነት በንፅፅር ካሳየ በኋላ፣ በገላትያ 4፡31 ውስጥ እንዲህ ይጠቀልለዋል፡

*ስለዚህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ የጨዋይቱ ልጆች ነን እንጂ የባሪያይቱ አይደለንም። (ገላትያ 4፡31)*

ልክ ይስሐቅ ከሳራ በአብርሃም እምነት ምክንያት እንደተወለደ ሁሉ፣ በእግዚአብሔር ተስፋዎች ማመን ለክርስቲያኖች የመዳን መንገድ ነው፡፡ ልክ እንደ አብርሃም ዘመን ሁሉ፣ በየዘመናቱ የሚገኙትም አማኞች የሚጸድቁት፣ በተስፋው ውስጥ የሚካተቱትና የጽድቅን ኑሮ የመኖርን አቅም የሚያገኙት በእግዚአብሔር ተስፋዎች በመታመን እንጂ በራሳቸው ጥረት አይደለም፡፡

አማኞች የእግዚአብሔርን በረከቶች በጠቅላላ ሊቀበሉ የሚችሉት በእምነት ብቻ ነው የሚለውን የጳውሎስን ማብራሪያ ለመመልከት አራቱን ዋና መከራከሪያዎቹን ተመልክተናል፡፡ የገላትያ ሰዎች አስቀድሞ የነበራቸውን የድነት ልምምድ በማንሳት፣ የአብርሃምን እምነት በመጥቀስ፣ የገላትያ ሰዎች ደስታቸውን የጣሉበትን የአሁን ልምም እና የአብርሃምን ሚስቶችና ወንዶች ልጆች ዘገባ በመጥቀስ ተሟግቷል፡፡

## ተግባራዊ ማሳሰቢያ

ምዕራፍ 1-4 ያለውን ይዘት በልቡናችን አድርገን፣ አሁን ደግሞ በ 5፡1-6፡10 የሚገኘውን ማሳሰቢያ ጠቅለል አድርገን እናያለን፡፡ ጳውሎስ በእነዚህ ምዕራፎች፣ የሐሰት መምህራኑ በገላትያ ውስጥ የፈጠሯቸውን በርካታ ተግባራዊ ችግሮች ይዳስሳል፡፡

ጳውሎስ በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ብዙ ተናግሯል እኛ ግን የጳውሎስን ሃሳብ በሦስት ዋና ርዕሶች ጠቅለል አድርገን እናቀርበዋለን፡ በ 5፡1-15 ኃላፊነት ያለበት በክርስቶስ የተገኘ ነጻነት፤ በ ገላትያ 5፡16-26 የመንፈስ ቅዱስ ኃይል እና በ 6፡1-10 የእግዚአብሔር ፍርድ ናቸው፡፡ አስቀድመን ጳውሎስ አፅንዖት የሰጠበትን ሃላፊነት ያለበት በክርስቶስ የተገኘ ነፃነት የተሰኘውን እንመልከት፡፡

## በክርስቶስ የተገኘ ነጻነት

ጳውሎስ በ 5፡1-15 ውስጥ የገላትያ ሰዎች በክርስቶስ ባገኙት ነፃነት በታማኝነት እንዲዘልቁ ጥሪ ያቀርባል፡፡ በዚህ ስፍራ ሚዛኑን በአግባቡ ጠብቋል፡፡ በመጀመሪያ፣ ክርስቲያናዊ ነፃነትን መጠበቅ እንደሚገባ አፅንኦት ሰጥቷል፡፡ በ 5፡1 የተናገረውን እናድምጥ፡

*በነጻነት ልንኖር ክርስቶስ ነጻነት አወጣን፤ እንግዲህ ጸንታችሁ ቁሙ እንደ ገናም በባርነት ቀንበር አትያዙ። (ገላትያ 5፡1)*

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

ጳውሎስ በመጀመሪያው ሚሲዮናዊ ጉዞው፣ አህዛብን ወደ ክርስትና እምነት ማለትም ከሸክም ነፃ ወደ መውጣት አምጥቷል፣ በነፃነታቸው እንዲዘልቁም ይፈልጋል ምክንያቱም የህገኝነት ሸክም እጅግ አደገኛና ከባድ ሸክም ስለሆነ ነው፡፡ በገላትያ 5፡2-3 እንዲህ ጽፏል፡

***እነሆ፥ እኔ ጳውሎስ እላችኋለሁ፦ ብትገረዙ ክርስቶስ ምንም አይጠቅማችሁም። ሕግንም ሁሉ እንዲፈጽም ግድ አለበት ብዬ ለሚገረዙት ሁሉ ለእያንዳንዶች ደግሜ እመሰክራለሁ። (ገላትያ 5፡2-3)***

በገላትያ የነበሩ የሐሰት መምህራን በሕገኝነት ይገኛል የሚሉትን የጽድቅ መንገድ ያስተዋውቁ ነበር፡፡ ክርስቲያኖች ከክርስቶስ ይልቅ በህግ ላይ እንዲታመኑ ያስተምሩ ነበር፡፡ ግን ያንን በማድረጋቸው፣ አህዛብ ክርስቲያኖችን ማንም ሊጠብቀው ወደ ማይችለው ስታንዳርድ ማለትም ህግን ሁሉ ወደ መፈፀም ቀንበር ውስጥ በግድ እየከተቷቸው ነበር፡፡ የነበራቸው ምርጫም በክርስቶስ ነፃ በመሆንና ለህግ ባርነት በመሰጠት መካከል ነበር፡፡ አንደኛው ወደ ድነት ሲያመራ አንዱ ግን ወደ ፍርድ ያመራል፡፡

ያም ሆኖ፣ ጳውሎስ በሁለተኛ ደረጃ፣ ክርስቲያናዊ ነፃነት፣ ክርስቲያን ግብረ-ገባዊ ሃላፊነትም እንዳበት የሚያረጋግጥ መሆኑን የሚሳየውን ሚዛኑን ያቀርባል፡፡ በአይሁድ ትውፊት እንደሚነገረው ክርስቲያናዊ ነፃነት የእግዚአብሔርን ግብረ-ገባዊ ህግጋት ማቃለል እንደሆነ እንዳይቆጥሩ የገላትያ ሰዎችን ያስጠነቅቃል፡፡ በ 5፡13 እንዲህ ጽፏል፡

***ወንድሞች ሆይ፥ እናንተ ለአርነት ተጠርታችኋልና፤ ብቻ አርነታችሁ ለሥጋ ምክንያትን አይስጥ፥ ነገር ግን በፍቅር እርስ በርሳችሁ እንደ ባሪያዎች ሁኑ። (ገላትያ 5፡13)***

ክርስቶስ የገላትያ ክርስቲያኖችን ጽድቅን ለማግኘትና የጽድቅን ሕይወት ለመኖር ኃይልን የመቀበያ መንገድ ተደርጎ ይቆጠር ከነበረው ከህግ እስራት ፈትቷቸዋል፣ ሆኖም ደግሞ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት እንዲከተሉ ይጠብቅባቸዋል፡፡ የገላትያ ሰዎች ከመገረዝ ነፃ መውጣታቸው የሕጉ መሠረት የሆነውን የእግዚአብሔር የተቀደሰ ባህርይ ለመዳፈር ነፃ እንዳደረጋቸው እንዲያስቡ ጳውሎስ አይፈልግም፡፡

## የመንፈሱ ኃይል

በክርስቶስ ስለተገኘው ነጻነትና ስለ ተቀደሰ ኑሮ አስፈላጊነት መሠረታዊ የሆኑ መንታ ግንዛቤዎችን ካሰፈረ በኋላ፣ ጳውሎስ በማስከተል በገላትያ 5፡16-26 ውስጥ የመንፈስ ቅዱስን ኃይል አስፈላጊነት ይዳስሳል፡፡ በህገኝነትና በሰብዓዊ ጥረት ካልሆነ የገላትያ ሰዎች ኃጢአትን መቋቋም እንዴት ይችላሉ?

ጳውሎስ ማንኛውም ክርስቲያን ለጽድቅም ሆነ የተቀደሰ ሕይወት ሕይወት ለመኖር የሚያስችል ኃይል ለመቀበል ሊታመን የሚገባው በመንፈስ ቅዱስ እንጂ በሥጋ እንዳልሆነ በአንድ ቃል መልስ ይሰጣል፡፡ በ5፡16 እና 25 መልስ የሰጠበትን መንገድ አድምጡ፡

***ነገር ግን እላለሁ፥ በመንፈስ ተመላለሱ፥ የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ። በመንፈስ ብንኖር በመንፈስ ደግሞ እንመላለስ። (ገላትያ 5፡16-25)***

ከጳውሎስ አመለካከት አንፃር፣ በክርስቶስ የተቀደሰ ሕይወት መኖር የሚቻልበት ብቸኛ መንገድ በእግዚአብሔር መንፈስ መታመንና በእርሱ መደገፍ ነው፡፡

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

አንድ ነገር ዘወትር ልብ ማለት የሚገባን ግን፣ ጳውሎስ መቼም ቢሆን መንፈስ ቅዱስን ከቅዱሳት መጻሕፍት በላይ ወይም ተፃራሪ አድርጎ ተመልክቶ እንደማያውቅ ነው፡፡ ለጳውሎስ፣ በመንፈስ መመላለስ ማለት ከተጻፈው መገለጥ መፋታት ማለት አይደለም፡፡ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ህዝብ ዘወትር የሚመራው እንደተፃፈው እንደ እግዚአብሔር ቃል ማለትም በብሉይ ኪዳን አስቀድሞ እንደተገለጠው፣ በአዲስ ኪዳን ደግሞ በጳውሎስ መልእክቶችና በሌሎችም የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ደረጃ በደረጃ በሚገለጠው አማካይነት ነው፡፡ በመንፈስ መመላለስ ማለት ግን ከተፃፈው ቃል ጋር ራስን ማስማማትም ብቻ አይደለም፡፡ እግዚአብሔር ያዘዘውን ትዕዛዝ ለመፈጸም ሙሉ በሙሉ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መታመንን ያካትታል፡፡ ክርስቲያኖች በሕይወታቸው የጽድቅን ፍሬ ለማፍራት በመንፈስ ቅዱስ እስከታመኑ ድረስ ከእግዚአብሔር ዘንድ ምንም ይመጣብናል ብለው መፍራት የለባቸውም፡፡

## መለኮታዊ ፍርድ

በሦስተኛ ደረጃ፣ ጳውሎስ እነዚህን ተግባራዊ ጉዳዮች የደመደመው ስለ እግዚአብሄር ፍርድ በመናገር ነው፡፡ በ 6፡7-9 ያስተላለፈውን ብርቱ ማስጠንቀቂያ አድምጡ፡

> ***አትሳቱ፤ እግዚአብሔር አይዘበትበትም። ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳልና፤***
> ***በገዛ ሥጋው የሚዘራ ከሥጋ መበስበስን ያጭዳልና፥ በመንፈስ ግን የሚዘራው ከመንፈስ የዘላለምን ሕይወት ያጭዳል።***
> ***ባንዝልም በጊዜው እናጭዳለንና መልካም ሥራን ለመሥራት አንታክት። (ገላትያ 6፡7-9)***

ጳውሎስ የገላትያ ሰዎች የፍፃሜ ዕጣ ፈንታ በብርቱ ያሳስበዋል፡፡ በክርስቶስ ያመኑ እውነተኛ አማኞች ድነታቸውን ምንም እንደማይነካው ያውቃል፡፡ ሆኖም ግን አማኝ ነኝ ያለ ሁሉ እውነተኛ እምነት እንደማይኖረውም ያውቃል፡፡ ስለዚህ፣ የገላትያ አብያተክርስቲያናት የሚመጣውን የእግዚአብሔርን ፍርድ እንዳይዘነጉ ያስጠነቅቃቸዋል፡፡ ተስፋ የሚያደርገውም ማስጠንቀቂያው ለመዳናቸው በክርስቶስና በመንፈስ ቅዱስ ላይ መታመንን እንዲመርጡ እንደሚያስችላቸው ነው፡፡

ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች የጻፈውን መልእክት ከዳሰስንበት ከዚህ አጭር ዳሰሳ፣ ጳውሎስ በገላትያ የነበሩ የሐሰት መምህራንን በብዙ መንገድ እንደተፋለመ ማየት እንችላለን፡፡ የገላትያ ሰዎችን በጣም ግላዊ በሆነ መንገድ ይለምናቸዋል፣ በእውነተኛው ወንጌል እንዲያምኑና ከዓመታት በፊት በሰበከላቸው በዚያው ወንጌል እንዲኖሩም ያሳስባቸዋል፡፡ በአጭሩ፣ ጳውሎስ የገላትያ ሰዎች የሐሰት መምህራንን እንዳይቀበሉ እና ጽድቅ በእምነት እንጂ በሥራ አይደለም የሚለውን እውነተኛ ወንጌል አጥብቀው እንዲይዙ ያሳስባቸዋል፡፡

እስከዚህ ድረስ፣ ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች የጻፈውን መልእክት ዳራ እና የደብዳቤውን መሠረታዊ ይዘት መርምረናል፡፡ አሁን ደግሞ ሦስተኛውን ርዕሳችንን ማለትም የገላትያ መጽሐፍ የጳውሎስን ነገረ-መለኮታዊ አመለካከት እንዴት እንደሚንጸባርቅ የምንመለከትበት እርከን ላይ ደርሰናል፡፡

# 4. ነገረ-መለኮታዊ አመለካከት

ከዚህ ተከታታይ ትምህርታችን በመጀመሪው ትምህርት በጳውሎስ መልእክቶች ውስጥ በተላለፉ ትምህርቶችና ባሰመረበት ነገረ-መለኮታዊ ስልት መካከል ያለውን ልዩነት መመልከታችንን ታስታውሳላችሁ፡፡ በገላትያ የነበሩ

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

የሐሰት መምህራን አህዛብ ክርስቲያኖች እንዲገረዙ ያቀረቡትን ጥሪ ጳውሎስ በተደጋጋሚ እርማት ሰጥቶበታል፡፡ እናም ስለ መገረዝና ጽድቅ በእምነት ስለ መሆኑ ለማስረዳት ጠቀም ያለ ጊዜ ወስዶ ማብራሪያ ሰጥቷል፡፡

ጳውሎስ ስለ መገረዝና ስለ ድነት ያቀረባቸው ቀጥተኛ መግለጫዎች የመሠረታዊ ነገረ-መለኮታዊ ቁርጠኝነቱ መግለጫዎች ናቸው፡፡ በገላትያ መጽሐፍ ያስተማረው ትምህርት የነበረው የነገረ-ፍፃሜ አመለካከት ማዕከላዊ ሃሳብ ተዛምዶ ነው፡፡ ምንም እንኳን ኃጢአትና ሞት ክርስቶስ ዳግመኛ በክብር እስኪመለስ ድረስ ፈጽሞ ባይወገዱም፣ መጪው ታላቅ ዘመን በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ እንደጀመረ ጳውሎስ ምን ያህል እንደሚያምን ታስታውሳላችሁ፡፡ እናም ይህ ማለት ክርስቲያኖች ሊኖሩ የሚገባቸው "የተጠናቀቀና ገና የሚጠበቅ" ብለን በምንጠራው ዘመን ውስጥ ሲሆን ያም ዘመን ኃጢአትና ሞት ከዘላለም ድነታችን ጋር አብረው የሚኳዙበት ዘመን ነው፡፡

ሆኖም የአሁን ዘመንና መጪው ዘመን በተኳዳኝ አብረው መኳዛቸው በገላትያ ውስጥ አንዳንድ አደገኛ የግንዛቤ መዛባቶች እንዲያቆጠቁጡ አስችሏቸዋል፡፡ የገላትያ ሰዎች መገረዝን፣ ጽድቅን እና የመሳሰሉትን አስመልክቶ የገቡበት ውዝግብ የሌላ መሠረታዊ ችግር ምልክት እንደሆነ ጳውሎስ ያምናል፡፡ በገላትያ የነበረው እጅግ መሠረታዊ ስህተት ክርስቶስ በሞቱና በትንሣኤው መጪውን ዘመን እንደጀመረው የሐሰት መምህራኑ እጅግ ዝቅተኛ ግምት መስጠታቸው ነበር፡፡ የመጪው ዘመን አብዛኛው ነገር አሁን እዚህ በገሃድ እየተከናወነ እንደሆነ መገንዘብ አልቻሉም፡፡ በውጤቱም፣ ይህንን የሀሰት ትምህርት "ነገረ-ፍፃሜን አለመረዳት" ብለን ልንጠራው እንችላለን፣ ያም ማለት አመለካከታቸው የክርስቶስን የመጀመሪያ መምጣት አኮስሶታል ማለት ነው፡፡

እንግዲህ በአንድ በኩል፣ ጳውሎስ የሐሰት መምህራኑን "ነገረ-ፍፃሜን አለመረዳት" በገላትያ መጽሐፍ በሁሉም ክፍሎች ውስጥ ጥቃት ፈጽሞበታል፡፡ ሆኖም እኛ ጳውሎስ በዚህ ችግር ረገድ ማእከላዊ ነገረ-መለኮታዊ አመለካከቱን ተግባራዊ ባደረገባቸው ስድስት ጉዳዮች ላይ እናተኩራለን፡፡ በመጀመሪያ፣ ስለ ክርስቶስ የሰጠው መግለጫ፤ ሁለተኛ፣ በወንጌል ላይ ያደረገወ ትኩረት፤ ሦስተኛ፣ የሙሴ ሕግ፤ አራተኛ፣ ከክርስቶስ ጋር የመተባበራችን አስተምህሮ፤ አምስተኛ፣ መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ሕይወት ስላለው ድርሻ የሰጠው አጽንዖት እና ስድስተኛ፣ ስለ አዲሱ ፍጥረት አስተምህሮው የሰጠው የመጨረሻ ይግባኝ ናቸው፡፡

## ክርስቶስ

ጳውሎስ ስለ መጨረሻው ዘመን ያቀረበው ይግባኝ በገላትያ መጽሐፍ መግቢያ ውስጥ ስለ ክርስቶስ በሰጠው መግለጫ በግልፅ ተቀምጧል፡፡ በገላትያ 1፡3-4 ጳውሎስ ኢየሱስን እንዴት እንደገለፀው አድምጡ፡

> ***ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታችንም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን። ከፉ ከሆነ ከአሁኑ ዓለም ያድነን ዘንድ እንደ አምላካችንና እንደ አባታችን ፈቃድ ስለ ኃጢአታችን ራሱን ሰጠ። (ገላትያ 1፡3-4)***

ጳውሎስ የገላትያ ሰዎች በረከትን ከአብና ከክርስቶስ እንዲቀበሉ ምኞት ብቻ አልተመኘላቸውም፡፡ ይልቁኑ፣ አብ ክርስቶስን ወደ ላከበት ዓላማ አትኩሮት ያደርጋል፡፡ በዚህ ስፍራ እንዳስቀመጠው፣ ኢየሱስ የተላከው "ክፉ ከሆነ ከአሁኑ ዓለም ያድነን ዘንድ" ነው ይላል፡፡

"ክፉ የሆነ የአሁኑ ዓለም" የሚለው መግለጫ በአግባቡ ከምናውቀው ከአይሁድ አገላለጽ ጋር ተዛማጅነት ያለው መግለጫ ነው፡፡ "ክፉ የሆነ የአሁኑ ዓለም" መሲሁ ከመምጣቱ አስቀድሞ ከነበረው የኃጢአትና የፍርድ ዘመን ከሆነው "የአሁን ዘመን" ጋር ተወራራሽ ነው፡፡ ጳውሎስ ክርስቶስን በዚህ መንገድ የገለጸበት ምክንያት የገላትያ

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

ሰዎች ክርስቶስ ወደ ምድር የመጣበትን ዓላማ፣ ማለትም ክርስቲያኖችን ለመጪው ዘመን ነጻ አውጥቶ ለማዘጋጀት የሚለውን ዋና ነገር እንደሳቱ ገና በደብዳቤው መግቢያ ላይ ለማመልከት ነው፡፡

በገላትያ የነበሩ የሐሰት መምህራን ክርስቶስ ለዓለም ያመጣውን ለውጥ በርካታ ክርስቲያኖች እንዳያስተውሉ አድርገዋቸዋል፡፡ ይህም በገሃድ የታየው የሐሰት መምህራኑ ዘመን ወዳለፈበት የኪዳን ምልክት ወደ ኋላ እንዲመለሱ በሚያደርጉት ውትወታ ነው፡፡ ኢየሱስ ወደ ምድር የመጣው አማኞችን ከዚህ ዘመንና ከአሮጌ መንገዶቹ ነፃ ሊያወጣ እንደሆነ የክርስትና እምነት ያስተምራል፡፡ ይህንን እውነት በፅንሰ-ሃሳብም ሆነ በተግባር መካድ የክርስትናን እምነት መሠረታዊ ነገር መካድ ነው፡፡

## ወንጌል

የገላትያ ሰዎች ለነገረ-ፍፃሜ የሰጡትን አነስተኛ ስፍራ አስመልክቶ ጳውሎስ ያለውን ስጋት የገለፀበት ሁለተኛ መንገድ ከሐሰት መምህራኑ ጋር የማይስማማው ጉዳዩ ከ"ወንጌል" ጋር ስለተያያዘ መሆኑን በመግለጽ ነው፡፡ በገላትያ 1፡6-7 ጳውሎስ ጉዳዩን ጠቅለል አድርጎ ያቀረበበትን መንገድ አድምጡ፡

> ***በክርስቶስ ጸጋ እናንተን ከጠራችሁ ከእርሱ ወደ ልዩ ወንጌል እንዲህ ፈጥናችሁ እንዴት እንዳለፋችሁ እደነቃለሁ፤***
> ***እርሱ ግን ሌላ ወንጌል አይደለም፤ የሚያናውጡአችሁ የክርስቶስንም ወንጌል ሊያጣምሙ የሚወዱ አንዳንዶች አሉ እንጂ። (ገላትያ 1፡6-7)***

በገላትያ የነበሩ የሐሰት መምህራን ስለ ኢየሱስ መናገራቸውን እንዳላቆሙ በእርግጠኝነት መናገር እንችላለን፡፡ አሁንም ክርስቲያን ነን ነው የሚሉት፡፡ ታዲያ፣ ጳውሎስ መልእክታቸውን ልዩ ወንጌል ወይም ወንጌል አይደለም የሚለው ለምንድን ነው?

የዚህን ዐረፍተ-ነገር ወሳኝነት ለመጨበጥ፣ "ወንጌል" ወይም "የምሥራች" የሚለውን ቃል ማስታወስ ይገባናል፣ አንዳንድ ጊዜ እነደሚተረጎመው፣ ቃሉ የተገኘው *euangelion* (euvangge,lion) ከተሰኘው የግሪክ ቃል ነው፡፡ ይህ የአዲስ ኪዳን የግሪክ ቃል በብሉይ ኪዳኑ የዕብራይስጥ ቃል *mebasar* ላይ፣ በተለይም በኢሳያስ ጥቅም ላይ በዋለው ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ነቢዩ ኢሳያስ በ52፡7 ላይ የተናገረውን አድምጡ፡

> ***የምስራች የሚናገር፥ ሰላምንም የሚያወራ፥ የመልካምንም ወሬ የምስራች የሚናገር፥ መድኃኒትንም የሚያወራ፥ ጽዮንንም፡- አምላክሽ ነግሦአል የሚል ሰው እግሩ በተራሮች ላይ እጅግ ያማረ ነው። (ኢሳያስ 52፡7)***

በዚህ ምንባብ፣ ኢሳይያስ የሚናገረው የብሉይ ኪዳኑ የእስራኤል ግዞት ስለሚያበቃበት ዘመን ነው፡፡ የሚጠቀመውም ቃል "የምሥራች" የሚለውን ሲሆን ያም ግዞቱ እንደሚያበቃ የሚነገረውን አዋጅ ለመግለጽ፣ ማለትም እግዚአብሔር በሰው ታሪክ ውስጥ መንግሥቱን እንደሚመሠርት እና እግዚአብሔር በጠላቶቹ ላይ እንደሚፈርድ ህዝቡንም እንደሚባርክ መነገሩ ነው፡፡ ኢሳይያስ በዚህ ስፍራ እንደተናገረው፣ የድነቱ የምሥራች "አምላክሽ ነግሦአል" ያም የእግዚአብሔር ንግሥና ነው፡፡ ከግዞቱ በኋላ የእግዚአብሔር ንግሥና በአዲስ ኪዳን እንደተገለጠው "የእግዚአብሔር መንግሥት" ወይም በሌላ አገላለጽ "መጪው ዘመን" ተብሎ ተገልጧል፡፡

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

እንግዲያው፣ የሐሰት መምህራኑ “ወንጌል ጨርሶ የላቸውም” ብሎ ጳውሎስ ሲናገር፣ ሊያመለክት የፈለገው ክርስቶስ መጪውን ዘመን፣ የድነትን ዘመን፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት ዘመን ማምጣቱን የካዱ መሆኑን ነው፡፡ የሐሰት መምህራኑ መገረዝን በማስተማር ደግሞም ህግን በመፈጸም በሥራ መጽደቅን ሲያውጁ፣ የክርስቶስን የመጀመሪያ መምጣት እውነተኛ ወሳኝነት መካዳቸው ነው፡፡ ክርስቶስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ወይም መጪውን ዘመን ወሳኝ በሆነ መንገድ እንዳመጣ ስለማያምኑ፣ የሚነገር የምሥራች ወይም ወንጌል የላቸውም፡፡ አሁንም እንደገና፣ የገላትያ መሠረታዊ ችግር የሐሰት መምህራኑ ነገረ-ፍፃሜን በትክክል አለመገንዘባቸው እንደሆነ ጳውሎስ ተረድቷል፡፡ የክርስቲያኖች ወንጌል ክርስቶስ በእርግጥም የእግዚአብሔርን መንግሥት ወደ ምድር ማምጣቱን እና መጪውን ዘመን ማብሰሩን የሚያውጅ ነው፡፡

## ህግ

የጳውሎስ ነገረ-ፍፃሜ ለገላትያ ሰዎች በጻፈው ደብዳቤ ላይ ተጽእኖ ማሳደሩን የምናይበት ሦስተኛ መንገድ በሙሴ ህግ ላይ ያቀረበው ዳሰሳ ነው፡፡ ጳውሎስ በዚህ ደብዳቤ ውስጥ የህግን ርዕሰ ጉዳይ ደጋግሞ አንስቷል፣ በምዕራፍ 3 ግን ከአሁኑ ዘመንና ከመጪው ዘመን ጋር በተገናኘ መንገድ በግልጽ ዳሰሶታል፡፡

እንግዲህ፣ የእግዚአብሔርን በረከቶች በእምነት መቀበል ጳውሎስ በአህዛብ የወንጌል አገልግሎት ውስጥ ያካተተው አዲስ ትምህርት እንዳልሆነ ተመልክተናል፡፡ በቅዱሳት መጻሕፍት በጠቅላላ እምነት የመዳን መንገድ ሆኖ ዘልቋል፡፡ ሆኖም ጳውሎስ በእምነት ላይ የሰጠው አጽንዖት ብርቱ ጥያቄ አስነስቷል፡ ለአይሁድም ሆነ ለአህዛብ የእግዚአብሔር በረከቶች የሚገኙት በእምነት ከሆነ፣ የሙሴ ህግ ዓላማው ምንድን ነው? እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ሙሴን ህግ ለምን ሰጣቸው? ጳውሎስ በ3፡19 ውስጥ ለእነዚህ ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣል፡

> ***እንግዲህ ሕግ ምንድር ነው? ተስፋው የተሰጠው ዘር እስኪመጣ ድረስ በመካከለኛ እጅ በመላእክት በኩል ስለ ሕግ መተላለፍ ተጨመረ። (ገላትያ 3፡19)***

ጳውሎስ እንዴት እንዳስቀመጠወ ልብ በሉ፡፡ ህጉ የተሰጠው “በመተላለፍ ምክንያት ነው” ደግሞም “ዘሩ እስኪመጣ ድረስ” ነው፡፡

መጀመሪያ ስንመለከተው፣ ጳውሎ የሙሴን ህግ ግብረ ገባዊ ጠቀሜታ ወደ ጎን ገለል ያደረገው ማለትም ከክርስቶስ መምጣት አስቀድሞ ከነበረው ዘመን ጋር ብቻ ያገናኘው ይመስላል፡፡ ይህ እንዳልሆነ ግን በገላትያ ውስጥ የሚገኙ በርካታ ምንባቦች ያረጋግጣሉ፡፡ በገላትያ 5፡14 አማኞች ፍቅርን መከታተል ለምን እንደሚያስፈልጋቸው ጳውሎስ ከዘሌዋውያን 19፡18 በመጥቀስ ማሳመኛ ያቀርባል፡

> ***ሕግ ሁሉ በአንድ ቃል ይፈጸማልና፥ እርሱም፦ ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ የሚል ነው። (ገላትያ 5፡14)***

ተመሳሳይ የሆነው ከህግ ጋር የተጣቀሰው ማሳመኛ በገላትያ 5፡22-23 ይገኛል፡

> ***የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ እምነት፥ የውሃት፥ ራስን መግዛት ነው።***
> ***እንደዚህ ያሉትን የሚከለክል ሕግ የለም። (ገላትያ 5፡22-23)***

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

ክርስቲያኖች የሙሴን ህግ ወዲያ እንዲጥሉ ጳውሎስ ያላስተማረ ከሆነ፣ በገላትያ 3፡19 ውስጥ ህጉ የተሰጠው “በመተላለፍ ምክንያት ነው”፣ የሚሠራውም “ዘሩ እስኪመጣ ድረስ ነው” ብሎ ለምን ጻፈ?

ይህንን ጥያቄ ለመመለስ፣ በገላትያ የነበረው ችግር ማለትም የሐሰት መምህራኑ ህጉን ከሚገባው በላይ አግዝፈው ያስተምሩ ስለነበር እንዲያስተውሉ ለማገዝ ነበር፡፡ ህጉን መታዘዝ ከእግዚአብሔር ዘንድ ድነትን ለመቀበል ያስችላል ብለው ያስተምሩ ነበር፡፡ ጳውሎስ ግን እግዚአብሔር ዘወትር ህዝቡን የሚባርከው በእምነት ብቻ እንደሆነ ያስተምራል፡፡ በ3፡19 ውስጥ ህጉ የተሰጠው “በመተላለፍ ምክንያት ነው” ያለው ለዚህ ነበር፡፡ ህጉ የተደነገገው ለህዝቡ ድነትን ለመስጠት ወይም የተቀደሰ ሕይወት የመኖር አቅም እንዲሆናቸው አልነበረም፡፡

ሆኖም ግን ዘሩ በእግዚአብሔር ቅድ ውስጥ “ዘሩ እስኪመጣ ድረስ” ያም ማለት ክርስቶስ እስኪመጣ ድረስ እጅግ ወሳኝ ድርሻ ነበረው፡፡ የሙሴ ህግ የተሰጠው ወንዶችንና ሴቶችን ስለ ኃጢአታቸው ለመኮነን ነበር፡፡ ሆኖም ግን የህጉ የመኮነን ሥልጣን ጊዜያዊ ነበር፡፡ አሁን ግን ክርስቶስ መጥቷል፣ አዲሱንም ዘመን አብስሯል አማኞችም ከክርስቶስ ጋር በመተባበራቸው ምክንያት፣ በሚመጣው ዘመን ውስጥ እንዲገቡ ተደርገዋል፡፡ በሚመጣውም ዘመን ኃጢአትን የመኮነን የሕጉ ሥልጣን ተሽሯል፡፡ የክርስቶስ እውነተኛ ተከታዮች ከህግ እርግማን ነፃ ናቸው፡፡

# ከክርስቶስ ጋር መተባበር

የጳውሎስ መልእክት ስለ ነገረ-ፍፃሜ በነበረው ማዕከላዊ አመላካከት ላይ የተደገፈ መሆኑን የምንመለከትበት አራተኛ መንገድ፣ አማኞች ከክርስቶስ ጋር ስለመተባበራቸው በሰጠው ትኩረት ነው፡፡ በገላትያ የነበሩ የሐሰት መምህራን የገላትያን ሰዎች ያበረታቱ የነበሩት ድነታቸውን ከግል ነገር ጋር ብቻ አያይዘው እንዲያስቡት ነበር፡፡ በመገረዝ ላይ ማትኮራቸውና የሙሴን ህግ እንዲጠብቁ ማስገደዳቸው አንድ ሰው የተቀደሰ ሕይወት ለመኖር ጉዳዩን ሁሉ ወደ ግል ጥረቱ እንዲመለሰው፣ ጽድቅንም ህግን በመታዘዝ፣ በሥራ እንዲሸምት የሚያደርግ ነበር፡፡ በውጤቱም፣ ወንዶች፣ ሴቶችና ልጆች በእግዚአብሔር ፊት የሚቆሙት የግል ሥራቸውን ብቻ ይዘው ነው ማለት ነው፡፡

ጳውሎስ ግን እንደሚያሳስበው ጽድቅም ሆነ የተቀደሰ አኗኗር በዚህ መንገድ ጨርሶ ሊገኝ አይችልም፡፡ ጽድቅና የተቀደሰ ሕይወት ሊገኝ የሚችለው ከክርስቶስ ጋር በመተባበር ብቻ ነው፡፡ በገላትያ 3፡26-29 ጳውሎ እንዲህ በማለት ያስቀምጠዋል፡

> ***በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና፤***
> ***ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋልና።***
> ***አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፥ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፥ ወንድም ሴትም***
> ***የለም፤ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና።***
> ***እናንተም የክርስቶስ ከሆናችሁ እንኪያስ የአብርሃም ዘር እንደ ተስፋውም ቃል ወራሾች***
> ***ናችሁ። (ገላትያ 3፡26-29)***

በገላትያ የነበሩ የሐሰት መምህራን እንደሚያስቡት በቤተክርስቲያን ውስጥ አንዳንዶቹ ክርስቲያኖች ከሌሎቹ በልጣሉ ምክንያቱም እያንዳንዱ ሰው በእግዚአብሔር ፊት የሚቆመው እንደ ሥራው መጠን ስለሆነ ነው፡፡ ይህ አስተሳሰባቸው ግን የተሳሳተ ነው፡፡ እውነቱ ግን፣ “ክርስቶስን መልበሳችን ነው”፣ እኛ “በክርስቶስ ውስጥ ነን”፡፡ ከክርስቶስ ጋር በዚህ መንገድ አንድ ስለሆንን፣ እግዚአብሔር ክርስቲያኖችን የሚያቸው በክርስቶስ ውስጥ ነው፡፡ እናም ክርስቶስ ፍጹም ጻድቅና ቅዱስ በመሆኑ፣ ደግሞም የአብርሃምን በረከቶች ሁሉ ሊቀበል የተገባው ስለሆነ፣

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

እግዚአብሔር እኛንም የሚያየን በእርሱ አማካይነት ጻድቃንና ቅዱሳን ደግሞም በረከቶቹን ሁሉ ሊቀበሉ እንደተገባቸው አድርጎ ነው፡፡

የጳውሎስ አመለካከት የመነጨው ከነገረ-ፍፃሜያዊ ግንዛቤው መሆኑን እንደገና እናሰምርበታለን፡፡ በጳውሎስ አስተምህሮ መሰረት ከዚህ ከፍርድ ዘመን ወደሚመጣው የበረከት ዘመን ሽግግር የተደረገው በክርስቶስ ሕይወት፣ ሞትና ትንሣኤ አማካይነት ነው፡፡ እርሱ ህጉን ፈፅሞ በመታዘዙ፣ ህጉ ከአማኞች የሚጠብቀውን ሁሉ ፈፅሞታል፡፡ በአማኞች ምትክ ሆኖ በመሞቱ የህጉን እርግማን በእነርሱ ምትክ ሆኖ ተቀብሏል፡፡ ኃጢአት የሞት ፍርድ የሚገባወ በመሆኑ ክርስቶስ በሞቱ የህጉን መስፈርት አሟልቷል፡፡ በአማኞች ምትክ ሆኖ ከሞት በመነሣቱም፣ ክርስቶስና እርሱ የሞተላቸው ሁሉ ክብር ሚገባቸው ሆነው በአብ ፊት ተቆጥረዋል፡፡ በውጤቱም፣ አማኞች ከክርስቶስ ጋር በእምነት ሲተባበሩ፣ እግዚአብሔርም ክርስቶስን በሚያይበት ዐይን ያያቸዋል፣ በዚህም መሠረት እነርሱ ከክርስቶስ ጋር ለህግ እርግማን ሞተዋል ደግሞም በሚመጣው ዘመን ለሚጠብቃቸው አዲስ ሕይወትም ከክርስቶስ ጋር ተነሥተዋል፡፡

በገላትያ ይኖሩ የነበሩ የሐሰት መምህራንን መከተል ማለት ክርስቶስ ለአብርሃም ተስፋ የተሰጠ ዘራቸው የመሆኑን ማዕከላዊ ሥራ ማቃለል ማለት ነው፡፡ በእነርሱ አስተምህሮ መሠረት በረከትንና የጽድቅን ኑሮ በሰብዓዊ ጥረት ለማግኘት መፈለግ ማለት ነው፡፡ ጳውሎስ ግን ክርስቶስን የሚያየው የድነት የትኛውም ገፅታ ተሟልቶ የሚገኝበት፣ አማኞችም የእግዚአብሔርን በረከቶች በጠቅላላ ሊቀበሉ የሚችሉት ከእርሱ ጋር አንድ ሲሆኑ እንደሆነ ሁሉን ግልጽ ያደረገ የአብርሃም ዘር አድርጎ ነው፡፡

# መንፈስ ቅዱስ

ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች የጻፈው መልእክት በነገረ-ፍፃሜያዊ አስተሳሰቡ የተቃኘ መሆኑን የምንመለከትበት አምስተኛ መንገድ መንፈስ ቅዱሰ በአማኞች ሕይወት ስለሚኖረው ሚና ያቀረበው ዘገባ ነው፡፡ እንዲያውም፣ ጳውሎስ ደብዳቤውን ሲጽፍ በልቡናው ከነበሩ አንኳር ሃሳቦ አንዱ የመንፈስ ቅዱስ ሚና ነው፡፡ ይህም አጽንዖት ጳውሎስ በገላትያ ስለነበረው የሐሰት አስተምህሮ መግለጫ በሰጠበት የመጀመሪያ ክፍል ውስጥ ይታያል፡፡ በገላትያ 3፡1-3 የጻፈውን አድምጡ፡

> ***የማታስተውሉ የገላትያ ሰዎች ሆይ፥ በዓይናችሁ ፊት ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ተሰቀለ ሆኖ ተሥሎ ነበር፤ ለእውነት እንዳትታዘዙ አዚም ያደረገባችሁ ማን ነው?***
> ***ይህን ብቻ ከእናንተ እንድማር እወዳለሁ፤ በሕግ ሥራ ወይም ከእምነት ጋር በሆነ መስማት መንፈስን ተቀበላችሁን?***
> ***እንዲህን የማታስተውሉ ናችሁ? በመንፈስ ጀምራችሁ አሁን በሥጋ ትፈጽማላችሁን? (ገላትያ 3፡1-3)***

የክርስትና ሕይወትን በመንፈስ ቅዱስ ላይ በመደገፍ ጀምረው የነበሩ የገላትያ ሰዎች፣ በሰብዓዊ ጥረታቸው ወደ መደገፍ እንዴት ዘወር ሊሉ እንደቻሉ ጳውሎስ በጣም ገርሞታል፡፡

ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ ሥራና በሥጋ ሥራ መካከል ትልቅ ትኩረት ከሰጠባቸው ክፍሎች መካከል አንዱ በገላትያ 5፡16-26 ያለው ክፍል ነው፡፡ በዚም በሥጋና በመንፈስ ሥራዎች መካከል ትልቅ ቅራኔ ያለ መሆኑን አሳይቷል፡፡ ጳውሎስ የኃጢአተኛን ተፈጥሮ ወይም የሥጋን ሰብዓዊ ጥረት እና የመንፈስን ፍሬ በተቃርኖ አስቀምጧል፡፡ በገላትያ 5፡19-21 የሥጋን ሥራዎች፣ ማለትም ዝሙት፣ ርኩሰት፣ መዳራት፣ ጣዖትን ማምለክ፣

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

ሟርት፣ ጥላቻ፣ ጠብ፣ ቅናት፣ ቁጣ፣ ራስ ወዳድነት፣ መለያየት፣ አድመኝነት፣ ምቀኝነት፣ ስካር፣ ዘፋኝነት፣ እንደሆኑ ገልጧል፡፡ በገላትያ 5፡22-23 ግን የመንፈስ ቅዱስን ፍሬ ማለትም፣ ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ ታማኝነት፣ ገርነት፣ ራስን መግዛት ነው ብሎ ገልጧል፡፡

የሐሰት መምህራኑ ግን በሥጋ ሰብዓዊ ጥረት ማለትም ራሳቸውን ለመገረዝ አሳልፈው በመስጠት የተቀደሰን ሕይወት መምራት የሚችሉበትን ኃይል እንዲያገኙ ይፈልጋሉ፡፡ ጳውሎሰ በዚህ ስፍራ እንዳሳየወ ግን፣ ሰብዓዊ ጥረት ሊያመጣ የሚችለወ ነገር ቢኖር ኃጢአት ብቻ ነው፡፡ እግዚአብሐየር በሚመጣው ዘመን በብሉይ ኪዳን አድርጎ በማያውቅበት ሁኔታ መንፈስ ቅዱስን እንደሚፈስስ በግልፅ ከተነገሩ ትንቢቶቸ መሃል ኢዮኤል 2፡28 ይጠቀሳል፡

> ***ከዚህም በኋላ እንዲህ ይሆናል፤ መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ፥ ሽማግሌዎቻችሁም ሕልምን ያልማሉ፥ ጐበዞቻችሁም ራእይ ያያሉ፤ (ኢዩኤል 2፡28)***

መንፈስ ቅዱስ ክርስቶስ ከመምጣቱም አስቀድሞ ነበር፣ አማኞች ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆነው እንዲዘልቁ ብርታትን ይሰጣቸውም ነበር፡፡ ሆኖም በዚያን ዘመን ሙላቱና ልዩ ስጦታዎቹ፣ እጅግ የተመጠኑና፣ በተወሰኑ ሰዎች ላይ ማለትም፣ በነቢያት፣ በካህናት እና በነገስታት ላይ ብቻ የሚገለጡ ነበሩ፡፡ በዚህ ረገድ፣ በብሉይኪዳን የመንፈስ ቅዱስ ኀልዎት፣ ትዕይንታዊና አግራሞትን የሚፈጥር ተዓምር ነበር፡፡ ሆኖም ኢዩዔል በትንቢቱ በሚመጣው ዘመን መንፈስ ቅዱስ በሁሉም አማኞች ላይ እንደሚፈስስ ተናግሯል፡፡ በሐዋርያት ሥራ 2 እንደምንመለከተውም፣ በበዓለ ሃምሳ ቀን የኢዩዔል ትንቢት መፈፀም ጀምሯል፡፡ በዚያን ወቅት፣ አስደናቂ በሆነ መንገድ እግዚአብሔር መንፈሱን በአማኞቸ ሁሉ ላይ አፍስሷል፣ ያም የሚያመለክተው የሚመጣው ዘመን እውን መሆን መጀመሩን ነው፡፡

በገላትያ ግን፣ የገላትያ ሰዎች የተቀደሰን ሕይወት ለመምራት በራሳቸው ሰብዓዊ ጥረት እንዲታመኑ የሐሰት መምህራኑ ይጎተጉቷቸዋል፣ ይህም በአዲስ ኪዳን ዘመን የመንፈስ ቅዱስ የተትረፈረፈ ስጦታና የማስቻል አቅም መካድ ነው፡፡ ክርስቶስ መጪውን ዘመን ሲያበስር ያስገኘውን የመንፈስ ቅዱስን ትልቅ በረከት መገንዘብ ተስኗቸዋል ማለት ነው፡፡ ስለዚህም ጳውሎስ፣ የክርስቶስ የሆኑት ሁሉ የመንፈስ ቅዱስን ኃይል በሙላት ተቀብለዋል በማለት የገላትያን ሰዎች ያሳስባቸዋል፡፡ የክርስቶ ተከታዮች በመንፈሱ ኃይል ሲታመኑ፣ የጽድቅን ፍሬ ለማፍራት በውስጣቸው ይንቀሳቀሳል፡፡

# አዲስ ፍጥረት

ጳውሎስ በነገረ-ፍፃሜ አስተምህሮው ላይ እጅግ የተደገፈ መሆኑን የምናስተውልበት የመጨረሻው ነጥብ ስለ አዲስ ፍጥረት ያነሳው ሃሳብ ነው፡፡ ይህ አስተምህሮ የሚገኘው በደብዳቤው ማብቂያ ላይ ነው፡፡ ጳውሎስ በገላትያ 6፡15-16 ያስቀመጠበትን መንገድ አድምጡ፡

> ***በክርስቶስ ኢየሱስ አዲስ ፍጥረት መሆን ይጠቅማል እንጂ መገረዝ ቢሆን ወይም ***
> ***አለመገረዝ አይጠቅምምና።***
> ***በዚህም ሥርዓት በሚመላለሱ ሁሉ ላይ በእግዚአብሔር እስራኤልም ላይ ሰላምና ምሕረት ***
> ***ይሁን። (ገላትያ 6፡15-16)***

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

በብዙ መንገዶች፣ ከላይ የተጠቀሱት ቃላት በገላትያ መጽሐፍ ውስጥ የተዘረዘሩትን አመለካከቶች ሰብስበው ይዘዋል፡፡ በጳውሎስ አመለካከት መሠረት፣ ተቃዋሚዎቹ መገረዝን ያለልክ ስፍራ ሰጥተውታል ምክንያቱም በክርስቶስ መምጣት አንድ ሰው መገረዙም ሆነ አለመገረዙ ፋይዳቢስ ሆኗልና፡፡ ይልቁኑ፣ ዋናው ነገር እያንዳንዱ ሰው "አዲስ ፍጥረት" የመሆኑ ጉዳይ ነው፡፡

ጳውሎስ *eschaton* ወይም የመጨረሻው ዘመን በክርስቶስ የመጀመሪያ መምጣት ተጀምሯል ማለትም ክርስቶስ ፍጥረተ ዓለሙን በጠቅላላ ወደ አዲስ ፍጥረትነት የመለወጥ የተሃድሶ ሥራውን ጀምሯል ብሎ እንደሚያምን ታስተውላላችሁ፡፡ እነዚህ የአዲስ ሥርዓት ጅማሬዎች ለእግዚአብሔር ህዝብ ታላቅ በረከትን አስገኝተዋል ያም የአሮጌውን ተፈጥሮ የቀደሙ መንገዶች ያስወገዱ ናቸው፡፡ ክርስቶስ ከመምጣቱ አስቀድሞ ወደነበረው የሕይወት ዘይቤ ከመመለስ ይልቅ፣ እያንዳንዱ አማኝ ግድ ሊለው የሚገባው በአዲስ ፍጥረትነት የመኖሩ ጉዳይ ነው፡፡ ከጳውሎስ ዘመን አንስቶ ክርስቶስ እስኪመለስ ድረስ፣ የክርስቶስ ተከታዮች ዋነኛ ናፍቆት በአዲሱ ፍጥረት የሚኖረው ሕይወት ነው፡፡ ጳውሎስ እንዳስቀመጠውም፣ ይህንን ምርጫቸው ያደረጉ ሰዎች በእርግጥም እነርሱ "የእግዚአብሔር እስራኤል" ናቸው፡፡

# 5. ማጠቃለያ

በዚህ ትምህርት በገላትያ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ተነስተው ለነበሩ ችግሮች ጳውሎስ እንዴት ምላሽ እንደሰጣቸው ተመልክተናል፡፡ በገላትያ የነበሩ የሐሰት መምህራንን ዳራ ዳስሰናል፣ ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች የጻፈውን መልእክት ይዘት ተመልክተናል በመጨረሻም በገላትያ የነበረውን ችግር ለመፍታት ጳውሎስ በነገረ-ፍፃሜያዊ አስተምህሮው ማዕከላዊ ሃሳብ እንዴት እንደተደገፈ አይተናል፡፡

ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች የሰጠውን ምላሽ ስንመለከት፣ በእነርሱ ብርቱ ችግሮች ዙሪያ እንዴት መመሪያ እንደሰጣቸው ብቻ ሳይሆን፣ ዛሬም ለእኛ ጳውሎስ እንዴት እንደሚናገረን እናያለን፡፡ በየዘመናቱ የሚነሱ ክርስቲያኖች በየወቅቱ እንደ ገላትያ ሰዎች ይኖራሉ፡፡ የክርስቶስ የመጀመሪያ መምጣት የሰው ዘርን ታሪክ እንዴት እንደቀየረው እንዘነጋለን፡፡ ልክ እንደ ገላትያ ሰዎች ኢየሱስ ጥቂት ብቻ እንደሠራ በመቁጠር ወደራሳችን አታካጭ የኑሮ ዘይቤ ዘወር እንላለን፡፡ የጳውሎስ ማዕከላዊ ነገረ-መለኮት ለገላትያ ሰዎች የጠቀማቸውን ያህል ለእኛም በእጅጉ ይጠቅመናል፡፡ በሚመጣው ዘመን በረከቶች ውስጥ እንኖር ዘንድ ክርስቶስ ከፉ ከሆነው ከአሁኑ ዓለም አውጥቶናል፡፡ በክርስቶስ ኢየሱስ ወደተገኘው ወደ አዲሱ ፍጥረት መንገዶች ልባችንን ስንመልስ፣ የክርስቶስ ወንጌል በእውነትም የምሥራች ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ክርስቶስ ድነትን ለዓለም ይዞ መጥቷል ዛሬም ቢሆን በዚያ የመዳን በረከት ውስጥ የመኖር ዕድል ተሰጥቶናል፡፡

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org